# የዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት በአዝማሪ አንደበት

መስፍን መሰለ[1]


### አኅጽሮተ ጥናት

የዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንት የሚያሞግሱ በአዝማሪ የተደረደሩ ግጥሞች ቢኖሩም የተመራማሪዎችን ትኩረት ግን አላገኙም፡፡ በጽሑፍ የተመዘገበውን መነሻ በማድረግ የዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት በአዝማሪ አንደበት እንዴት እንደተገለጸ የሚያስረዳ ጥናት አለመኖር ይኸን ጥናት ማካኼድ አስፈላጊ ኾነ፡፡ የጥናቱ ዓላማ ደጅ አዝማች ካሣ (ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ) በጀግንነታቸው በአዝማሪ እንዴት እንደተሞገሱ መመርመር ነው፡፡ ሙገሳው የዐመጽ ዘመናቸውንና ዳግማዊ ዐጼ ቴዎድሮስ ተብለው የኢትዮጵያን አንድነት ለመመሥረት በተለያዩ ግዛቶች (በደንቢያ፣ በሰሜን፣ በትግራይ፣ በወሎ፣ በሸዋና በጎጃም) የነበሩትን መሳፍንት ድል ማድረጋቸውንና ምኞታቸውን የሚገልጹ ናቸው፡፡ በጥናቱም የደጅ አዝማች ካሣ/ዐፄ ቴዎድሮስ ድሎች፣ የፈጸሟቸው ድርጊቶች፣ ውጣ-ውረዶች በአዝማሪ አንደበት እንዴት እንደተገለጹ ተመርምረዋል፡፡ በሙገሳ ግጥሞቹ የሚገለጸው ሐሳብ በታሪክ ከተመዘገበው ታሪካቸው ጋር ምን ያኽል እንደሚጣጣም ለማገናዘብ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይኸ ጥናት በተመራማሪዎች ብዙም ትኩረት ያልተደረገበትን የደጅ አዝማች ካሣ (የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ) ጀግንነት በአዝማሪ አንደበት መሞገሳቸውን በመመርመር ክፍተቱን ያጠበዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከታሪክ መጻሕፍት፣ ከመጽሔቶች፣ ከጋዜጦችና ከዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕሎች ነው፡፡ ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንነት የሚያሞግሱት በአዝማሪ የተደረደሩ ግጥሞች ተሞጋሹ በሕይወት ዘመናቸው ከፈጸሟቸው ድርጊቶች ጋር ግንኙነት አላቸው፡፡ የጥናቱ ውጤት ለፎክሎርና ለታሪክ ተመራማሪዎች ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡


ቁልፍ ቃላት፡- [ካሣ/ቴዎድሮስ፣ አዝማሪ፣ ጀግንነት፣ ሙገሳ]

## 1) **ታሪካዊ ዳራ**[2]

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በበጌምድር፣ በጎጃም፣ በሰሜን፣ በትግራይ፣ በወሎና በሸዋ እየተዘዋወሩ፣ አንድነትን ለመመሥረት ጥረት አድርገዋል፡፡ ከመንግሥታቸው መቀመጫ ደብረ ታቦር ርቆ ወደሚገኘው ሸዋ ሦስት ጊዜ ዘምተው ከፍተኛ ጦርነት አካኺደዋል (Darkwah, 1969) ፡፡ ውጣ ውረድ በበዛበት የንግሥና ዘመናቸው "አንዱ አሜን ብሎ ሲገባ ሲሾም፣ ሌላው ሲሸፍት ሲያዝ፣ ሲታሰር፣ ሲፈታ፣ ሲያመልጥ፣ ያመለጠውም ሲያዝ ሲገደል" (ተክለ ጻድቅ፣ 1981፤ 162) ጊዜያቸውን ያለ እረፍት አሳለፉ፡፡ ተቀናቃኞቻቸውን ለመቅጣትና ለማስገበርም ያለ እረፍት ያካኼዷቸውን ዘመቻዎች በአብዛኛው በድል አጠናቅቀዋል፡፡ ይኸም ደፋር ጀግና ለመባል አብቅቷቸዋል፤ በአዝማሪ አስሞግሷቸዋል፡፡ የመሞገሳቸው ምክንያት አዝማሪ ለነገሥታቱ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ቅርበት ስለነበረው ነው፡፡ ድርጊቶችን በግጥም የመግለጽ ችሎታው፣

[1] በዐድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ የፎክሎርና ሥነጽሑፍ ተመራማሪ፡፡

[2] ይኸ ጥናት አኹን በቀረበበት ቅርጽና ይዘት እንዲታተም ለማድረግ በስም የሚታወቁና የማይታወቁ ሰዎች አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበርና ይመሰገናሉ፡፡

የማዝናናት አቅሙ፣ በጦርነት ወገንን የመቀስቀስ፣ ጠላትን የማኮሰስ ብቃቱ በነገሥታቱና በመሳፍንቱ የመቀጠር ዕድል ያስገኝለታል፡፡ ይኽን ዕድል ያገኘ አዝማሪ ጌታው በበቅሎ ወይም በፈረስ በሚያደርገው አድካሚ ጉዞ ከሌሎች አሽከሮች ጋር በእግሩ ይከተላል፡፡ በመንገድ ላይ ወይም በሚታረፍበት ወይም በሚታደርበት ቦታ በምግብ ሰዓትም፣ ከምግብ በኋላም ጌታውንና ታዳሚዎቹን ያዝናናል፤ ያሞግሳል፤ ግለሰብን ይተቻል (Ashenafi, 1975)፡፡ አዝማሪ ወደ ጦርነት የሚደረግን ዘመቻ ያጅባል፤ ወደ ፍልሚያ የሚገባውን ተዋጊም በጀግንነት እንዲዋጋ ያበረታታል፡፡ ከዘመቻ የሚመለስን ጦር በመሰንቆ አድምቆ ይቀበላል (ገነት፣ 2009)፡፡

አዝማሪ በመሳፍንቱና በመኳንንቱ የግብር ሥርዓትና ግብዣ ላይ በመገኘት ታዳሚዎችን ያዝናናል (አስቴር፣ 2007፤ 189)፡፡ አዝማሪ ዘፈን በመከወን ሰውን ከማዝናናቱ ባሻገር በኢትዮጵያ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሥፍራ ነበረው፡፡ የአዝማሪ ዋና ሥራ ማዝናናት ቢኾንም ዜናና ታሪክ ይነግራል፤ ይተቻል፤ ፖለቲካ ይተነትናል፤ ይዘግባል፤ አዝማች ኾኖ ያገለግላል (Kimberlin, 1976; Ashenafi, 1975)፡፡ አዝማሪ ጀግናንና ጀግንነትን፣ ማኅበረሰብንና መልካም ጓደኝነትን ያሞግሳል፤ ጌታውንም፣ ጓደኞቹንም እንዲኹም የጌታው ጠላቶች ተገቢ ያልኾነ ባሕርይና ድርጊት ይተቻል (Kimberlin, 1976)፡፡ የሙገሳ ግጥሞችን በመደርደር የታዳሚዎችን ቀልብ ወደ ተፈጸሙ ድርጊቶች በትውስታ ይወስዳል፡፡ በሕይወት ያሉትንና የሌሉትን የጌታውን የቅርብ ዘመዶች፣ ጓደኞች እንዲሁም የራሱን ወዳጆች ስምና መልካም ተግባራት እየዘረዘረ ያሞግሳል፤ ይዘክራል፡፡ የጌታውን ተቀናቃኞች በሌሉበት ያኰስሳል፤ ይሰድባል፤ ይወቅሳል፡፡ ግጭት ሊፈጠር እንደሚችል ይነግራል፤ ግጭት ሲፈጠርም፣ የጌታውንና የነፍጠኞቹን ጀግንነት ከፍ ከፍ እያደረገ፤ የጌታውን ተቀናቃኝ ደግሞ ያኰስሳል፤ ይሰድባል፡፡ ግጭቱ ጠንክሮ ጦር ወደ መማዘዝ ካመራም ለፍልሚያ ያነሣሣል፡፡ ፍልሚያው ወደሚካኼድበት ቦታ ከጌታው ጋር በመዝመትም፣ ደፋሮችን ያሞግሳል፣ ወላዋዮችን ለውጊያ ያተጋል፤ ፈሪዎችን ይነቅፋል፤ ይሰድባል፡፡ የፍልሚያው የቅስቀሳ ክፍል ኾኖ ይሠራል፡፡ በፍልሚያው ማን የጀግንነት ተግባር እንደፈጸመና  ጊዜው የሚጠይቀውን ግዴታ ማን እንዳልተወጣ ይመለከታል፡፡ ግዳይ እየጣሉ የሚፎክሩትን የጌታው አሽከሮች ተግባር በአእምሮው ይመዘግባል፡፡ ከፍልሚያው በኋላ በሚፈጠሩ ልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ለምሳሌ፣ በግብር የጀግንነት ተግባር የፈጸሙ ነፍጠኞችን ባሉበት ወይም በሌሉበት ሥራቸውን እየጠቀሰ ያሞግሳል፤ ፈሪዎችን ደግሞ ያኮስሳል፡፡

ጦርነትን ድል አድርጎ የተመለሰ ንጉሥ በቤተ መንግሥቱ አዳራሽ ለመኳንንቱና ለሠራዊቱ ግብር ማብላት የተለመደ የኢትዮጵያ ባህል ነበር፡፡ በግብሩም ላይ አዝማሪው የጦርነቱን ውሎ እያወሳ የጠላትን ስም እያራከሰ የንጉሡንና የሠራዊታቸውን ዝና እያነሣሣ ማሞገስ የተለመደ ነበር (ተክለ ጻድቅ፣1981)፡፡  በቤተ መንግሥት ለእንግዳ ግብር በሚቀርብበት ጊዜም የቤተ መንግሥቱ ምርጥ አዝማሪ በእራት ግብዣው ላይ በመገኘት ዐፄ ቴዎድሮስንና እንግዳቸውን ያዝናና ነበር፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከምፅዋ ወደ ጎንደር ለመጣው የእንግሊዝ ቆንስል የእራት ግብዣ ባደረጉበት ዕለት አዳራሽ የተገኘውን አዝማሪያቸው እንዲያጫውታቸው መጋበዛቸው አዝማሪውም ልዩ ልዩ ግጥሞችን እየደረደረ ማዝናናቱ (ፉሴላ Fusella), 1959) አዝማሪ ለቤተ መንግሥቱ የነበረውን ቅርበት ይገልጻል፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ተለያዩ ቦታዎች ባደረጓቸው ዘመቻዎች አዝማሪ አብሮ ይዘምት እንደ ነበር የሚጠቁም ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በሰሜንና በትግራይ ሸፍተው የነበሩትን ደጅ አዝማች ንጉሤንና ወንድማቸውን ለማስገበር ባደረጉት ዘመቻ አዝማሪ አብሮ ዘምቷል፡፡ የዚኹ ማረጋገጫ በግጥም ላሚረቱባቸው ተቃዋሚዎቻቸው ንጉሡ በግጥም የሰጡትን መልስ እንዲነገር ያደረጉት በአዝማሪ ነው (ገሪማ፣ 1996)፡፡ ይኸም ቀደም ሲል እንደተገለጸው ዐፄ ቴዎድሮስ ተቀናቃኞቻቸውን ለማስገበር በዘመቱባቸው ቦታዎች ኹሉ አዝማሪ የዘመቻው አካል ነበር የሚል ፍንጭ ይሰጣል፡፡ ስለኾነም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ባካኼዷቸው ልዩ ልዩ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ከቅርባቸው ያልተለየው አዝማሪ አብተው በርካታ የሙገሳ ግጥሞችን ደርድሮላቸዋል፡፡ የልጅ ካሣን (ዐፄ ቴዎድሮስን) ጀግንነት የሚገልጹ በርካታ የቃል ግጥሞች በተለያዩ የታሪክና የግጥም መጻሕፍት፣ እንዲሁም በምርምር ሥራዎች ተመዝግበው ቢገኙም ተገቢው ጥናት አልተደረገባቸውም፡፡ በተበታተነ መንገድ በተለያዩ ሥራዎች ተመዝግበው የሚገኙትን የሙገሳ ግጥሞች አንድ ላይ በማድረግ ማጥናት አስፈላጊ የኾነበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው፡፡

የዚኽ ጥናት ትኩረት አዝማሪ ደጅ አዝማች ካሣን (ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን) ባሞገሰባቸው ቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ነው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣን የሚያኮስሱ፣ ባሕርያቸውን የሚገልጹ፣ ከሞቱ በኋላም በአልቃሽ የተንጎራጎሩ በአዝማሪ የተዜሙ ቃል ግጥሞች በዚኽ ጥናት ትኩረት አልተደረገባቸውም፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ ደጅ አዝማች (ዐፄ ቴዎድሮስ) በጀግንነታቸው በአዝማሪ የተሞገሱባቸውን ግጥሞች ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውዳቸውን መሠረት በማድረግ መመርመር፣ መተርጎምና መተንተን ነው፡፡ ከዚኽ ዋና ዓላማ የሚመነጩ ንዑስ ዓላማዎችም፣ 1) በሙገሳ ግጥሞቹ የተንጸባረቁትን ይዘቶች ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውዶች መሠረት በማድረግ መተንተን፣ 2) ደጅ አዝማች ካሣ/ዐፄ ቴዎድሮስ በተሞገሱባቸው ግጥሞች ጀግንነታቸው እንዴት እንደተንጸባረቁ ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውዳቸውን መሠረት በማድረግ መመርመርና መተንተን ናቸው፡፡ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካትም፣ 1) በሙገሳ ግጥሞቹ የተንፀባረቁት ኹነቶች ደጅ አዝማች ካሣ/ዐጼ ቴዎድሮስ ከፈጸሟቸው የጀግንነት ተግባሮች ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውዶች ጋር ምን ያኽል ይጣጣማሉ)? 2) ደጅ አዝማች ካሣ/ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተቀናቃኞቻቸውን ድል በማድረግ መቅጣታቸው በሙገሳ ግጥሞች እንዴት ተንጸባረቁ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን፡፡ ትንተናው የተካኼደው የሙገሳ ግጥሞቹ የተከወኑባቸውን ማኅበራዊና ታሪካዊ ዐውዶች መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹ ልጅ ካሣ ሸፍተው ሊወጓቸው የዘመቱባቸውን፣ ከነገሡ በኋላም ተቀናቃኞቻቸውን ድል ማድረጋቸውን የሚዘግቡ ናቸው፡፡ የደጅ አዝማች/ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት ዛሬም ድረስ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች በአዝመሪ እንደሚሞገስ ቢታወቅም ይኸ ጥናት ተመዝግበው በተገኙት የሙገሳ ግጥሞች ላይ የሚያተኩት ነው፡፡

በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድርስ ታሪክ ላይ በርካታ የምርምር ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ መጻሕፍትና መጣጥፎች ታትመዋል፡፡ ፓንክረስትና አስፋውም (1985) በዘመኑ የነበረ ሰው የመዘገባቸውን በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወታደሮች የተዜሙ የጦርነት ግጥሞችን ሰብስበውና ምንነታቸውን ገልጸው አሳትመዋል፡፡ አዳነች (2001) በበኩላቸው ለኹተኛ ዲግሪ መመረቂያቸው በተመረጡ

የታሪክ መጻሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ የተመዘገቡ የሥነቃል ዓይነቶችን ሲሰበስቡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን የሚመለከቱ የቃል ግጥሞችን ሰብስበዋል፡፡ እነዚኽ ጥናቶች ከዚኽ ጥናት ጋር ቀጥታ ግንኙነት የላቸውም፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኬኔዲና በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም አብያተ መጻሕፍት እንዲኹም በኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት የደጅ አዝማችን/የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንነት በሚያሞግሱ ግጥሞች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ጥናት አላገኘንም፡፡ ይኹን እንጂ እንደ አስፈላጊነታቸው በደጅ አዝማች/በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ የተደረጉ ሌሎች ጥናቶችን እንደ አስፈላጊነታቸው ለዚኽ ጥናት በማጠቀሻነት ተገልግለንባቸዋል፡፡

የደጅ አዝማች ካሣን/ዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንነትን የሚገልጹ በርካታ የቃል ግጥሞች በተለያዩ የታሪክና የግጥም መጻሕፍት፣ እንዲኹም በታሪክ ላይ ትኩረት ባደረጉ የምርምር ሥራዎች ተመዝግበዋል፡፡ ይኽ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው የደጅ አዝማች ካሣን/የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንነት በሚያሞግሱ የቃል ግጥሞች በመኾኑ እሳቸውን በሚያኮስሱ፣ ማንነታቸውን በሚገልጹ፣ ከሞቱ በኋላም በኀዘን እንጉርጉሮነት በአዝማሪ በተዜሙት ላይ ትኩረት አልተደረገም፡፡ ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ አዝማሪ የደረደረላቸውን የሙገሳ ግጥሞች ማጥናት የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ማንነትና የፈጸሟቸውን ድርጊቶች፣ በዘመኑ የነበረውን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ኢኰኖሚያዊ ኹኔታዎች፣ በጦርነት ጊዜ በአጥቂውና በተጠቂው ላይ የሚፈጠሩ ስሜቶችን እናውቅባቸዋለን፡፡ በታሪክ መረጃነት ማገልገላቸውንና በታሪክ መጻሕፍት ለታሪኩ ውበት፣ ተነባቢነት፣ ጭብጥ መጉላት፣ አይረሴነት አስተዋጽኦ እንዳላቸው እንገነዘብባቸዋለን፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹ ምን ያኽል ታሪካዊ እውነታውን እንደ ገለጹ እንረዳባቸዋለን፡፡

መረጃዎች የተሰበሰቡት ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች ነው፡፡ የቃል ግጥሞቹ የተሰበሰቡት ስለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተገጠሙ ግጥሞች ይገኙባቸዋል የተባሉ ሥራዎችን በማንበብ ነው፡፡ የመረጃ ምንጮቹ የተመረጡት በምቹ የናሙና አወሳሰድ (በይሁነኝ) ዘዴ ነው፡፡ መጻሕፍቱም፣ <u>አማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው</u> እና <u>ዝክረ ነገር</u> (ማኅተመ ሥላሴ፣ 1961፣ <u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> (ገሪማ፣ 1996)፣ የኢትዮጵያ ታሪክ (ሥርግው ገላው፣ 2008)፣ <u>ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት</u> (ተክለ ጻዲቅ፣ 1981) እና በተለያዩ ጊዜያት የታተሙ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕሎች[3] ናቸው፡፡[4] ከእነዚኽና ሌሎችም ምንጮች ከመቶ በላይ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን

[3]መረጃዎች የተሰበሰቡባቸው ሦስቱ የዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕሎች 1ኛ) ደብተራ ዘነብ ጽፈውት Enno Littmann (1902) ያሳተሙት፣ 2ኛ) ዐፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ ከዐሥራ ሦስት ዓመት በኋላ አለቃ ወልደ ማርያም የተባሉ የሸዋ ሰው የጻፉትና C. Mondon-Vidailhet (1904) ያሳተሙትና 3ኛ) ስማቸው ባልታወቁ ጸሓፊ ተጽፎ በ Luigi Fusella (1958, 1959) የታተመው ናቸው፡፡ ከእነዚኽ ሥራዎች የተገኙት መረጃዎች በዚኽ ጥናት ሲጠቀሱ ሊትማን (Littmann)፣ ቪዳሌ (Vidailhet) እና ፉሴላ (Fusella) በማለት በቅንፍ የተቀመጡትን ስሞች እንዲተኩ ተደርጓል፡፡ በመረጃ ጽሑፎች ግን የጸሓፊዎቹ ስም ከምንጩ በተገኘበት ቋንቋ ተጽፏል፡፡

[4]በዚኽ ዝርዝር ወስጥ ያልተካተቱ በአዝማሪ የተደረደሩ ጥቂት ቃል ግጥሞች የተገኙባቸውን ሥራዎች በምንጭነት ተጠቅመናል፡፡ ከዚኽ ሌላ፣ አንዳንዶቹ ጸሐፊዎች ከእነሱ ቀድመው ከታተሙ ሥራዎች ያገኟቸውን ቃል ግጥሞች፣ በአዝማሪ የተደረደሩትንም ጭምር መዝግበዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በተክለ ጻዲቅ (1981) ሥራ ውስጥ የተጠቀሱት ቃል ግጥሞች አብዛኛዎቹ እሳቸው በመረጃ ምንጭነት ከተገለገሉባቸው የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕሎች የተቀዱ ናቸው፡፡

በተለያየ መንገድ የሚገልጹ የቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡ የቃል ግጥሞቹ በተለያዩ የጥናት ርእሶች የሚመረመሩ ናቸው፡፡ ይኸ ጥናት ትኩረት ላደረገበት ርእሰ ጉዳይ ሠላሳ ያኸል የሙገሳ ግጥሞች የተሰበሰቡ ቢኾንም የተተረጎሙትና የተነተኑት ግን ዐሥራ አንድ ናቸው፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹ ለትንተና የተመረጡት ከጥናቱ ርእሰ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው በመኾኑ ነው፡፡ ለዚኽ ጥናት የተመረጡት አብዛኛዎቹ የሙገሳ ግጥሞች የተወሰዱት ከገሪማ (1996) መጽሐፍ ነው ፡፡ ይኸ የተደረገበት ምክንያት በምንጭነት ከተጠቀምንባቸው ሥራዎች ከኹሉም የበለጠ የሙገሳ ግጥሞች ተመዝግበው የተገኙት በእሳቸው ሥራ በመኾኑ ነው፡፡

በዚኽ ጥናት የቃል ግጥሞች፣ የሙገሳ ግጥሞች ሙገሳዎች እና መረጃዎች በማለት ለዋውጠን የጠራናቸውን ከታሪክ ነጥሎ መተርጎምና መተንተን አይቻልም፡፡ ይኹን እንጂ ይኽን የሥነ ቃል ዓይነት እንደ የቃል ታሪክ መረጃ መቁጠርና በቃል ታሪክ ንድፈ ሐሳብ (Oral History Theory) መተርጎምና መተንተን አልተሞከረም፡፡ ምክንያቱም በዚኽ ጥናት በመረጃነት የተጠቀምንባቸው መረጃዎች በጽሑፍ ተመዝግበው የተገኙና በቃል ታሪክ ንድፈ ሐሳብ የማይካተቱ መኾናቸው ነው፡፡ ይኽንን ግልጽ ለማድረግ በቃል ታሪክ ንድፈ ሐሳብ የሚዳኙት መረጃዎች ምን ዓይነት እንደኾኑ አብራምስና ቫንሲና በየሥራዎቻቸው በእንግሊዝኛ ያሉትን እንጠቅሳለን፡፡ Abrams (2010: 9) እንደሚሉት "Oral history exists in four forms: the original oral interview, the recorded version of the interview, the written transcript and the interpretation of the interview material." ("የቃል ታሪክ የሚኖረው በአራት ቅርፆች (forms) ማለትም በዐዲስና በተለየ የቃል ቃለ መጠይቅ፣ በድምፅ መቅጃ በተመዘገበ ቃለ መጠይቅ ዓይነት፣ ወደ ጽሑፍ በተቀየረ ቃለ መጠይቅ እና በተተረጎመ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡") Vansina (1985፡ 12) በበኩላቸው "The sources of oral historians are reminiscences, hearsay, or eyewitness accounts about events and situations which are contemporary, that is, which occurred during the lifetime of the informants." ("የቃል ታሪክ ባለሙያዎች መረጃዎች ትውስታዎች፣ የስሚ ስሚዎች ወይም ድርጊቶችና ኹኔታዎች በተፈጸሙበት ወቅት መረጃ ሰጭዎች በሕይወት እያሉ መፈጸማቸውን በዓይን እማኝነት የተመለከቱ ናቸው") ብለዋል፡፡ ኹለቱም የቃል ታሪክ ጥናት ባለሙያዎች እንደገለጹት በቃል ታሪክ ንድፈ ሐሳብ የሚመረመሩት መረጃዎች ካልአይ ናቸው፡፡ ይኽም ማለት መረጃዎቹ በቀጥታ ከመረጃ ሰጪዎች የሚሰበሰቡ እንጂ በዚኽ ጥናት የተገለገልንባቸው መረጃዎች ከሰነድ የተገኙ አይደሉም፡፡

በዚኽ ጥናት በመረጃነት የተጠቀምንባቸው የሙገሳ ግጥሞች ራሳችን ከመረጃ ሰጪዎች የሰበሰብናቸው ሳይኾኑ በጽሑፍ ተመዝግበው የተገኙ ናቸው፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹ በጽሑፍ ከመመዝገባቸው በፊት በአዝማሪ ሲከወኑ የቃል ግጥምን ባሕርያት ሊያሟሉ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል (በቃል መተላለፋቸው፣ በሚከወኑበት ጊዜ ሊሻሻሉ የሚችሉ መኾናቸው፣ በሚከወኑበት አጋጣሚ የከዋኝና የተሳታፊ መስተጋብር መኖሩ ወዘተርፈ)፡፡ በጽሑፍ ተመዝግበው የተላለፉትና ለእኛ የደረሱት በጽሑፍ በመኾኑ ከቃላዊነት ይልቅ የጽሑፍነት

ባሕርይ ይጎላባቸዋል፡፡ ተመዝግበው በተገኙበት ቅርጽ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋሉ፡፡ በምንም ምክንያት ሳይለወጡ፣ የከዋኙና የተሳታፊ መስተጋብር ተፅዕኖ ሳይኖርባቸው ለሌላ ትውልድ ይደርሳሉ፡፡ በዚኽ ጥናት የተጠቀምንባቸውን መረጃዎች ምን ብለን እንጥራቸው? የቃል ግጥምንና ተጽፎ የቀረበን ግጥም ለመለየት የሚያስችል ድንበር የለም ወይ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ በቅድሚያ በቃል በተነገረና በጽሑፍ በቀረቡ የፈጠራ ሥራዎች መካከል ድንበር ማበጀትን በተመለከተ Finnegan (1988፡ 178) የገለጹትን ቀጥለን እንመልከት፡፡

> 'Orality' and 'literacy' are not two separate and independent things; or (to put it more concretely) the oral and written modes are not two mutually exclusive and opposed processes for representing and communicating information. On the contrary they take diverse forms in differeing cultures and periods, are used differently in different social contexts and, insofar as they can be distinguished at all as separate modes rather than a continuum, they mutually interact and affect each other and the relations between them are problematic.
>
> *ቃላዊነትና ጽሑፋዊነት ኹለት የተለያዩና አንዱ በሌላው ላይ ጥገኛ ያልኾነ ማለት አይደለም፡፡ ወይም (በጣም በተጨባጭነት) የቃልና የጽሑፍ ቅጦች መረጃን በመያዝና በማስተላለፍ በኩል ኹለቱም አንዱ ሌላውን የማይጨምርና የሚቃረኑ ኺደቶች አይደሉም፡፡ በተቃራኒው በተለያዩ ባህሎችና ጊዜያቶች በተለያዩ ማኅበራዊ ዐውዶች የተለያየ አጠቃቀም ስለሚኖራቸው የተለያዩ ቅርፆችን ይይዛሉ፡፡ ስለኾነም በቀጣይነት እንደ ተለያዩ ቅጦች ተለይተው የሚታወቁ ከመኾን ይልቅ የእርስ በእርስ መስተጋብር ያላቸውና አንዱ በሌላው ላይ ተፅዕኖ ስለሚያደርግ በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ለመለየት አስቸጋሪነት አለው፡፡*

በቃላዊነትና በጽሑፋዊነት መካከል ልዩነት ለመፍጠር ቢያስቸግርም ለዚኽ ጥናት የተጠቀምንባቸውን መረጃዎች አዝማሪ በቃሉ በመከወን ያቀረባቸው በመኾኑ የቃል ግጥሞች ማለትን መርጠናል፡፡ ምክንያቱም በጽሑፍ ተመዝግበው መገኘታቸው በጽሑፍ የቀረበ ግጥም ባሕርይ እንዲጋሩ ቢያደርጋቸውም ቃላዊነት ተጸንሰው የተወለዱበትና ተግብራቸውን ያገኙበት ነው፡፡ በቃል ተደርሰው ለእኛ በጽሑፍ ሲደርሱ ከቃል ግጥም ባሕርያት ያጎደሉት ቢኖርም የሚዳኙት ግን ተግባር ላይ በዋሉበት ዐውድ ነው፡፡ ስለኾነም የሙገሳ ግጥሞቹን ለመተርጎምና ለመተንተን የቃል ታሪክ ንድፈ ሐሳብን መሠረት ከማድረግ ይልቅ ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውዳቸውን መሠረት በማድረግ መተርጎምና መተንተን ተመርጧል፡፡ ዐውዳዊ የትንተና ዘዴም ለቃላዊ የጥበብ ሥራ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት የተከወነበትን አጠቃላይ ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ኹኔታዊ (situational) ዐውዶች ግምት ውስጥ ማስገባት ነው (Ben-Amos, 1992:210)፡፡ ይኽ የትንተና ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በቃል የተከወነን የፎክሎር ዓይነት ትርጉም የተከወነበትን ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውድ እንዳያጣ ለማድረግ ስለሚያስችል ነው (Hufford, 1995)፡፡ ስለኾነም በዚኽ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው የሙገሳ ግጥሞች የተተረጎሙትና የተተነተኑት የተከወኑበትን

ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውድ መሠረት በማድረግ እንዲኾን ተደርጓል፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹ የተመረጡት በአዝማሪ መዜማቸውን የሙገሳ ግጥሞቹን በሥራዎቻቸው የመዘገቡ ሰዎች በአዝማሪ መዜማቸውን በመግለጻቸው ነው፡፡ ከደራሲዎቹ ማረጋገጫ መስጠት በተጨማሪ በኅብረተሰቡ ውስጥ አዝማሪ በማንኛውም አጋጣሚ ሲከውን የሰማቸውን የቃል ግጥሞች እሱ ለሚፈልገው አገልግሎት ለመጠቀም ባህሉ የሚፈቅድለት መኾኑ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡[5] በተመረጡት ሥራዎች ተመዝግበው የተገኙት የልጅ/የደጅ አዝማች ካሣ/የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንነት የሚያሞግሱ ግጥሞች በአዝማሪ እንደሚደረደሩ ቢታመንም የጽሑፎቹ ደራሲዎች በአዝማሪ ለመደርደራቸው ምስክርነት ባለመስጠታቸው በርካታዎቹ በመረጃነት አልተወሰዱም፡፡

አብዛኛዎቹ ጸሓፊዎች የሙገሳ ግጥሞቹን በአዝማሪ በተከወኑባቸው አጋጣሚዎች ላይ ተገኝተው አልመዘገቡም፡፡ አብዛኛዎቹ የሙገሳ ግጥሞችም የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ዜና መዋዕል በአካል ተገኝተው በጻፉት በአለቃ ዘነብ ሥራ ውስጥ አይገኙም፡፡ ጸሓፊዎቹ "በአዝማሪ የተዜሙ" ያሏቸውን የሙገሳ ግጥሞች የመዘገቡት ድርጊቶቹ ከተፈጸሙና ከተከወኑ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው (ስሙ ያልታወቀውን የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ጸሓፊ ጨምሮ)፡፡ ለዚኽም ማስረጃው፣ ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ የጻፉትና የሙገሳ ግጥሞችን በሥራዎቻቸው የመዘገቡት ሰዎች ንጉሡ ከሞቱ በርካታ ዓመታት በኋላ መኾኑ ነው፡፡ ጸሓፊዎቹ በሥራዎቻቸው ውስጥ የመዘገቧቸው የሙገሳ ግጥሞች ምንጭ፣ አንድም፣ ዐፄ ቴዎድሮስ በሕይወት በነበሩበት ዘመን የተደረደሩትን የሰሙ ሰዎች ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚያስተላልፉ ሰዎች ናቸው፡ ፡ አንድም፣ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ዓላማቸውንና ጀግንነታቸውን በማድነቅ አዝማሪ በተለያዩ ጊዜያት ሲደረድራቸው የሰሟቸውን አስታውሰው የመዘገቧቸው ናቸው፡፡

ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት አዝማሪ የደረደራቸው የሙገሳ ግጥሞች አብዛኛዎቹ በሠምና ወርቅ የተነገሩ ናቸው፡፡ ሠሙ በግጥሙ የተላለፈውን መልእክት መሸፈኛና ቀድሞ ለአእምሯችን ግልጽ የሚኾነው መልእክት ነው፡፡ ወርቁ ደግሞ በሠሙ ተደብቆ፣ ተሸፍኖ የሚነገረው የግጥሙ ውስጠ ምሥጢር ሙገሳው ነው፡፡ ሙገሳው በወርቁ የተነገረ በመኾኑ የትንተናው ትኩረት በወርቁ በተላለፈው መልእክት ላይ ነው፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹን መልእክት ለመረዳት ደጋግመን በማንበብ መርምረናል፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹን ይዘት ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውዳቸውን መሠረት በማድረግ ተተንትነዋል፡፡ ሠሙም፣ ወርቁም እንዴት እንደተገለጹ በማስረዳት የሙገሳ ግጥሞቹ ተተርጉመዋል፤ ተተንትነዋል፡፡ የተለያዩ ሰዎች በጥናቶቻቸውና በጉዞ ማስታዎሻዎቻቸው ስለ

[5]አዝማሪ አንድም፣ አንድን አጋጣሚ መነሻ በማድረግ ዕዳዲስ ቃል ግጥሞችን ይደርሳል፤ ይደረድራል፡፡ አንድም፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ በማንኛውም ሰው፣ በማንኛውም አጋጣሚ ላይ (በግብር፣ በሰርግ፣ በክርስትና፣ በለቅሶ፣ በሥራ ወዘተርፈ) ሲደረደሩ የሰማቸውን ቃል ግጥሞች ሳያሻሽል ያዜማል፡፡ አንድም፣ በተጠቀሱትና በሌሎችም አጋጣሚዎች ወይም የሰማቸውን የቃል ግጥሞች አሻሽሎ እና ለአጋጣሚው እንዲስማሙ አድርጎ ያቀርባል፡፡ ይኸን የሚያደርገው አዝማሪው ቀድሞ የሰማውን የሙገሳ ግጥም ለሚፈልገው አገልግሎት ለመጠቀም የሚኖርበት ኅብረተሰብ (የአማራ፣ የትግራይ፣ የኦሮሞ፣ የአገው ወዘተርፈ) ባህል መብት ስለሚሰጠው፣ ስለሚፈቅድለት ነው፡፡ ስለኾነም በኅብረተሰቡ ከሚደረደሩ ልዩ ልዩ የቃል ግጥሞች አብዛኛዎቹ በአዝማሪ በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ ሊዜሙ ይችላሉ፡፡ ይኸም የሙገሳ ግጥሞቹ በተሰበሰበባቸው ሥራዎች በአዝማሪ የተደረደሩ ቃል ግጥሞች እንደኾኑ ደራሲዎቹ የሰጡትን ምስክርነት አምኖ ለመቀበል ያስችላል፡፡

አዝማሪ ወይም ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የዘገቧቸውን እንደ አስፈላጊነቱ በትንተናው ውስጥ ጠቅሰናል፡፡ ቀጥለው በሚቀርቡት ንዑሳን ርእሶችም የሙገሳ ግጥሞቹን ትንተና በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

## 2) ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት በአዝማሪ የተዜሙ ሙገሳዎች ትንተና

የሙገሳ ግጥሞችን ከመተንተናችን በፊት በቅድሚያ ጀግና፣ ሙገሳና እና አዝማሪ ለሚሉት ቃላት ብያኔ ለመስጠት እንሞክራለን፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ መዝገበ ቃላት (2006፤ 488) ጀግና የሚለው ቃል ፍቺ “ለሀገር፣ ለወገን መስዋዕትነት ከፍሎ ጥሩ ተግባር ያከናወነ፣ ወኔ፣ ድፍረት በሚጠይቅ ኹኔታ ላይ ጀብዱ የሠራ” ሰው የሚል ፍቺ ተሰጥቶታል፡፡ በመዝገበ ቃላቱ ለቃሉ የተሰጠው ፍቺ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዘመናዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት ካድረጉት ትግል ጋር ሲነጻጸር እሳቸውን ጀግና የሚያስብላቸውን ተግባር ፈጽመዋል፡፡ ዘመነ መሳፍንትን ለማስወገድ የወሰዷቸው ርምጃዎች፣ የአመጹባቸውን ማሸነፋቸው፣ ወታደራዊ አደረጃጀትን በመለወጥ በደመወዝ እንዲተዳደርና የማዕረግ ተዋረድ እንዲኖረው ለማድረግ መጀመራቸው፣ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ለመገንባት መጣራቸው፣ የቤተ ክህነትን መንፈሳዊ አገልግሎት በተወሰኑ ካህናት ለመገደብ መሞከራቸውና የመሬት ይዞታቸውን ለመለወጥ ያደረጉት እንቅስቃሴ፣ ባርነትን ለማስቆም የወሰዱት ርምጃ፣ ወዘተርፈ የኢትዮጵያ የተሐድሶና የዘመናዊነት ጀማሪ ተደርገው እንዲታዩ አድርገዋቸዋል (Crummey, 1969)፡፡ ባሕሩ (፪ሺ፱፤ 31) እንዳሉት “የዘመናዊ አሠራር ሐሳቦቹን” ግብ ለማድረስ እንደ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ “በስፋትና ያለመታከት የጣረ ንጉሥ አልነበረም፡፡” ክራሚ ከዚኽ በላይ በተመለከተው ሥራቸው ሮቢንሰንን ጠቅሰው የዘመናዊ ኢትዮጵያ አባት የሚባሉት ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን የተባበረች፣ የጠነከረችና ተራማጁ መንግሥት ለማድረግ በማሰብ በኩል በዓለም ላይ የእሳቸው አቻ ከነበሩ መንግሥታት ኹሉ የበለጡ እንደ ነበሩ ገልጸዋል፡፡ ስለኾነም የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ አመጽ ከጀመሩበት ከቋራ ተነሥተው በተለያዩ መሳፍንት ይገዙ የነበሩትን ክፍላተ ግዛቶችና በንጉሥ ይገዛ የነበረውን ሸዋን በኀይላቸው ይዘው ማስገበራቸው በጊዜው የወሰዷቸው የቅጣት ርምጃዎች በአዎንታዊነት በሚተረጉሟቸው ሰዎች ዘንድ ጀግና የሚያስብሏቸው ናቸው፡፡ ቀጥለን ሙገሳ ለሚለው ቃል በምንሰጠው ብያኔም የጀግንነታቸው ልክ ምን እንደ ነበር ብያኔያችን እናጎለብታለን፡፡

ሙገሳ ለሚለው ቃል “ምስጋና፣ አድናቆትና ውዳሴ” በማለት በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ መዝገበ ቃላት (2006፤ 88) የተሰጠው ፍቺ በዚኽ ጥናት ካለው አገልግሎት ጋር የተጣጣመ ነው፡፡ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተግባሮች ለቃሉ በመዝገበ ቃላቱ ከተሰጠው ፍቺ ጋር ይስማማል፡፡ በማስረጃነት ሦስት ነጥቦችን እንመለከታለን፡፡ አንደኛ፣ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው በፊት መጀመሪያ ልጅ በኋላ ደግሞ ደጅ አዝማች ይባሉ በነበረበት ጊዜ ሽፍተው በወታደራዊ አቅማቸውና ማዕረጋቸው ከእሳቸው የሚበልጡትን በማሸነፋቸው ግርምትን አድናቆትን ለማግኘት አስችሏቸዋል፡፡ ኹለተኛ፣ ደጅ አዝማች ካሣ (ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ) የተለያዩ ክፍለ ግዛቶች ይገዙ የነበሩትን የዘመነ መሳፍንት አውራዎች በማሸነፍ በድኻው ላይ ይደርስ የነበረውን ልዩ ልዩ በደል በማስወገዳቸው እፎይታን ካገኘው ኅብረተሰብ ምስጋና

ተችሯቸዋል፡፡ ሦስተኛው ነጥብ ከኹለተኛው ነጥብ ጋር የሚገናኝና ተጨማሪ ተግባሮቻቸው የተገለጹበት ነው፡፡ ይኸውም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ፍትሕን ለማስፈን አበረታች ተግባሮችን መፈጸማቸው፣ ገበሬው በሰላም አርሶ እንዲበላ፣ ነጋዴውም በሰላም እንዲነግድ፣ ሌላውም የኅብረተ ሰብ ክፍል የእሱ በኾነው ላይ ኑሮውን እንዲመራና ተረጋግቶ እንዲኖር በተደጋጋሚ ማወጃቸው፣ ዘመናዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት መትጋታቸው፣ ከነበሩበት ዘመን ወደፊት ኼደው የሚያስቡ ተደርገው እንዲታዩና እንዲወደሱ አድርጓቸዋል፡፡ በደመወዝ የሚተዳደር ወታደራዊ ተቋም ለመመሥረትና ተሠሪን ለማስቀረት መጣራቸው፣ ለወታደሮቻቸው "የዐሥር አለቃ፣ ያምሳ አለቃ፣ የሺ አለቃ፣ የሚባሉ አዳዲስ የሥልጣን ተዋረድ" መመሥረታቸው (ባሕሩ፣ ፪ሺህ፤ 33) ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እንዲወደሱ አድርገዋቸዋል፡፡ ከዘመናት በኋላም በተለያዩ የታሪክ ተመራማሪዎች (ቀደም ሲል በገለጽናቸውና በሌሎችም) ለእሳቸው የተሰጠውን ውዳሴ ተጋርተዋል፡፡ መልካም ሐሳቦቻቸውና ተግባሮቻቸው በተደጋጋሚ እየተወሱ ትውልድ እንዲቀበላቸው ተደርጓል፡፡

የሙገሳ ግጥሞቹን የደረደረው አዝማሪ በባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ (መሰንቆ) እየታጀበ በመዝፈን ኑሮውን የሚመራ ሰው ነው፡፡ ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የሙገሳ ግጥሞችን የደረደረው አዝማሪ ይኽን ተግባር መፈጸም የቻለው ለእሳቸው ቤተ መንግሥት ቅርበት ስለነበረው ነው፡፡ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት አዝማሪ የሙገሳ ግጥሞችን ይደረድር እንደ ነበረው ኹሉ በደቡብ አፍሪካ በዙሉ ማኅበረሰብ መሪዎች፣ በምዕራብ አፍሪካ በዳሆሜ፣ በናይጀሪያ በሐውሳ ማኅበረሰብ እና በሌሎችም ሀገሮች ተመሳሳይ ተግባር የሚከውኑ ነበሩ (Finnegan, 1977)፡፡ በሌሎች ሀገሮች ለቤተ መንግሥት ሰዎች ውዳሴ ግጥም ደርዳሪዎች እንደነበሩት ኹሉ በኛም ሀገር ዘመናዊ የሙገሳ መቅረቢያ ዘዴዎች (ጋዜጣ፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዢን) ከመስፋፋታቸው በፊት አዝማሪ ከፍተኛ ሚና ነበረው፡፡

በዚኽ ንዑስ ርእስ የምንመረምረው ተሞጋሹ በሦስት የማዕረግ ስሞች መጠራታቸውን መሠረት አድርገን ነው፡፡ የመጀመሪያው የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ወንድ ልጆች የሚጠሩበት ልጅ የሚለው የማዕረግ ስም ነው፡፡ ኹለተኛው ልጅ የሚለው ማዕረግ ቀርቶ በቀድሞ ጊዜ የጦር የበላይ ሹም በሚጠራበት ደጃዝማች በሚለው የማዕረግ ስም የተጠሩበት ነው፡፡ ይኽ የማዕረግ ስም በራስና በፊታውራሪ መካከል የሚሰጥ የማዕረግ ስም ነው፡፡ የተሞጋሹ ሦስተኛውና ከፍተኛው የማዕረግ ስም ንጉሥ[6] የሚል ነው፡፡ ይኽ የማዕረግ ስም በዘውዳዊ አስተዳደር ዙፋን ላይ በመቀመጥ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተብለው ሀገር በመምራታቸው የተጠሩበት ነው፡፡ የማዕረግ ስሞቹ ለተሞጋሹ የተሰጧቸው በተለያዩ ጊዜያት ነው፡፡ ልጅ በሚለው የማዕረግ ስም በሚጠሩበት ጊዜ ከእሳቸው የበለጠ የማዕረግ ስም ያላቸውን የእቴጌ መነንን ምስለኔዎች በተለያዩ ጊዜያት ባካኼዷቸው ጦርነቶች አሸንፈዋል፡፡ ለደጅ አዝማችነት ማዕረግ ከበቁ በኋላም የፊታውራሪነት፣ የደጅ አዝማችነት፣ የራስነት (አማታቸውን) ማዕረግ በነበራቸው ሰዎች የሚመራን ጦር ድል

---

[6]የንጉሥነት ማዕረግ ያላቸው የተለያዩ አካባቢዎች መሪዎች ካሉ እነሱን እያስገበረና እያዘዘ የሚኖረውን ንጉሠ ነገሥት ብሎ መጥራት የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ ሸዋ በንጉሥ ምኒልክ፣ ጎጃም በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ይመሩ በነበረበት ጊዜ ዐፄ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት የሚለውን ሥልጣነ ማዕረግ ይጠቀሙ ነበር፡፡

አድርገዋል፡፡ ከነገሡ በኋላ ደግሞ ከእሳቸው በማዕረግ ከሚያንሱ የየአካባቢው መሳፍንትና መኳንንት ጋራ ተዋግተው ከማሸነፋቸውም በላይ በጥፋታቸው ቀጥተዋቸዋል፡፡ በአሸናፊነታቸውና በድል አድራጊነታቸው ጀግና ተብለዋል፡፡ በዚኽም አዝማሪ አመስግኗቸዋል፤ አድንቋቸዋል፤ አሞግሷቸዋል፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹ ካሣ፣ ቴዎድሮስና ታጠቅ የሚሉ መጠሪያዎች ታክለውባቸው የቀረቡ ናቸው፡፡ በጥናቱም ታሪካዊና ባህላዊ እውነታዎች በአዝማሪ ሙገሳ እንዴት እንደተገለጹ እንመለከታለን፡፡

የሙገሳ ግጥሞቹ በኹለት ንዑስ ርእሶች ሥር ተመርምረዋል፤ ተተንትነዋል፡፡ በመጀመሪያው ንዑስ ርእስ የተመረመሩት ሙገሳ ግጥሞች ልጅ በኋላ ደጅ አዝማች ካሣ ይባሉ በነበረበት ጊዜ በጎንደር ቤተ መንግሥት ላይ በማመጻቸው የተሰነዘሩባቸውን ወታደራዊ ጥቃቶች በመመከትና በማጥቃት በፈጸሟቸው የጀግንነት ተግባሮች ላይ ያተኩራሉ፡፡ ኹለተኛው ንዑስ ርእስ የሚያተኩረው በተለያዩ ቦታዎች የነበሩትን መሳፍንት አሸንፈው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተብለው ከነገሡ በኋላ ወደ አላሸነፏቸው መሳፍንትና በንጉሥ ወደ ሚመራው ሸዋ ዘምተው ድል በማድረጋቸውና በየጊዜው የተነሡባቸውን ተቃዋሚዎች በማሸነፋቸው በተሞገሱባቸው ላይ ያተኩራል፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹ በዘመን ቅደም ተከተል የተፈጸሙ ድርጊቶችን ቢገልጹም በትንተና ኺደት ወደ ኋላና ወደ ፊት መመልከት አስፈላጊ በመኾኑ በዚኽ ጽሑፍ ውስጥ ሙሉ በሙሉ የታሪክ ኺደትን ቅደም ተከተል በጠበቀ መንገድ አልቀረበም፡፡ ምርመራችን ልጅ/ደጅ አዝማች ካሣ በማመጻቸው በተለያዩ ጊዜያቶች ሊያጠቋቸው የዘመቱባቸውን ድል በማድረጋቸው በተሞገሱባቸው እንጀምራለን፡፡

## 2. 1) ለልጅ/ለደጅ አዝማች ካሣ የተዜሙ ሙገሳዎች ትንተና

በዚኽ ንዑስ ርእስ ልጅ ካሣ ኀይሉ በእቴጌ መነን ላይ በማመጻቸውና በመሸፈታቸው የተሰነዘሩባቸውን ጥቃቶች በመመከት ድል በማድረጋቸው የተሞገሱባቸውን ግጥሞች እንመረምራለን፣ እንተነትናለን፡፡ ምርመራችን ደንቢያንና ቋራን ይገዙ በነበሩት በራስ ዓሊ እናት በእቴጌ መነን ላይ ልጅ ካሣ ኀይሉ የፈጸሙትን አመጽ መነሻ በማድረግ አዝማሪ ባሞገሳቸው ግጥም እንጀምራለን፡፡ በአዝማሪ የተሞገሱበት ግጥም፡-

ለቴዬ [ለእቴጌ] መነን ሙላው ሲነሣ፤  
አንፈራጠጠ እምቢ አለ ካሣ፡፡ (Mitgeteilt, p. 33)

የሚል ነው፡፡ ልጅ ካሣን ያስሞገሳቸው ለእቴጌ መነን አክብሮት መንፈጋቸው፣ ንቀት ማሳየታቸው፣ ማመጻቸው "እንቢ" ማለታቸው ነው፡፡ ሙገሳውን ለመረዳት ግጥሙ የቀረበባቸውን "ሲ/ተነሣ፣ አንፈራጠጠና እምቢ አለ" የሚሉትን ቃላት ጽሑፋዊ (textual) እና ዐውዳዊ ፍቺዎች እንመረምራለን፡፡ ተነሣ የሚለው ግሥ በግጥሙ ባለው ዐውድ አክብሮትን ለመግለጽ ከተቀመጡበት ብድግ ማለትን፣ መቆምን ይገልጻል፡፡ ይኽ ፍቺ በዐማራው ኅብረተሰብና በቤተ መንግሥት በሚፈጸመው ባህላዊ አክብሮት አሰጣጥ ላይ ያተኩራል (ይኽ ዓይነት ባህል በሌሎች የኢትዮጵያ ኅብረተሰቦች ሊኖር እንደሚችል ይገመታል)፡፡ ይኸውም፣ በባህሉ ታናሽ ለታላቅ፣

ልጅ ለወላጅ፣ ንስሐ ልጅ ለንስሐ አባት፣ (ሚስት ለባል)፣ ሎሌ ለጌታው አክብሮቱን ለመግለጽ ከተቀመጠበት መነሣት የተለመደ ነው፡፡ አክባሪዉ ወደ ተቀመጠበት ቦታ (ቤት ውስጥም ይኹን ከቤት ውጭ)፣ ተከባሪው ሲኼድ፣ አክባሪው አክብሮቱን ለመግለጽ ከተቀመጠበት ይነሣል፡፡ በባህሉ ሊከበር ለሚገባው ሰው ከተቀመጠበት በመነሣት አክብሮት አለመስጠት በኹለቱ ሰዎች መካከል አለመግባባት መኖሩን ወይም ንቀት ማሳየትን ይጠቁማል፡፡

ከሙገሳ ግጥሙ ታሪካዊ ዐውድ መረዳት እንደሚቻለው እቴጌ መነን ልጅ ካሣ እና ሌሎች ሰዎች ወደ ተቀመጡበት ይኼዳሉ፡፡ ኹሉም ሲነሡ ልጅ ካሣ አንፈራጠው ከተቀመጡበት ሳይነሡ ይቀራሉ፡፡ ከተቀመጡበት በመነሣት አክብሮት መስጠት፣ ወይም ማሳየት በቤተ መንግሥትም የተለመደውን ተግባር ሳይፈጽሙ ይቀራሉ፡፡ ልጅ ካሣ ከተቀመጡበት በመነሣት ለእቴጌ መነን መስጠት የሚገባቸውን ክብር አለመስጠታቸው ከባህልና ከቤተ መንግሥት ሥርዓት ያፈነገጠ ድርጊት በጎንደር ቤተ መንግሥት መፈጸማቸውን ከሙገሳ ግጥሙ ዐውድ እንረዳለን፡፡ በዚኽም በእቴጌይቱም፣ በቤተ መንግሥቱም ላይ ትእቢት፣ ኩራትና ንቀት ማሳየታቸውን፣ ማኩረፋቸውንና ማመጻቸውን ገልጸዋል፡፡ ልጅ ካሣ አንፈራጠው በመቀመጥ ለእቴጌይቱ ተገቢውን ክብር አለመስጠታቸው ከፍተኛ ቅጣት እንደሚያስከትልባቸው እያወቁ ደፍረው ስሜታቸውን መግለጽ መቻላቸው ደፋር፣ ጀግና የሚያስብላቸውን ድርጊት እንደፈጸሙ ተቆጥሮ አስሞግሷቸዋል፡፡

አንፈራጠጠ የሚለው ቃል በግጥሙ ባለው ዐውድ እግርን ከፈት አድርጎና ቦታ አስፍቶ በመያዝ መቀመጥን ይገልጻል፡፡ በማንኛውም ጊዜ የተቀመጡበትን ቦታ ከሌላ ሰው ጋራ ተጋሩም አልተጋሩም አንፈራጥጦ መቀመጥ እንደ ትእቢትና እንደ ኩራት እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡ ሰዎች ባሉበት በተለይ ደግሞ መሳፍንቱ፣ መኳንንቱና ወይዛዝሩ በተገኙበት ቦታ አንፈራጥጦ በመቀመጥ ሌላ ሰው እንዳይቀመጥ መከልከል ከፍተኛ ነውር ነው፡፡ ከዚኽም በላይ ሊከበር የሚገባው ሰው አንፈራጥጦ ወደ ተቀመጠው ሰው ሲመጣ አክብሮቱን ለማሳየት ከተቀመጠበት መነሣት ይጠበቅበታል፡፡ ይኹን እንጂ በሙገሳ ግጥሙ እንደተገለጸው ልጅ ካሣና ሌሎች በስም ያልተገለጹ ሰዎች ወደ ተቀመጡበት ቦታ እቴጌ መነን በኼዱበት ጊዜ አንፈራጠው ከተቀመጡበት አክብሮትን ለመግለጽ ያልተነሡት ልጅ ካሣ ብቻ ናቸው፡፡ ይኽ ድርጊት ልጅ ካሣ በእቴጌ መነን ላይ በተደጋጋሚ የማመጻቸውን፣ እንቢ የማለታቸውን እውነት ይገልጻል፡፡

ልጅ ካሣ የተሞገሱበትን የአመጽ ተግባር ሦስት ጊዜ መፈጸማቸውን ከታሪካቸው እንረዳለን፡፡ የመጀመሪያው ሸፍትነታቸው[7] ምክንያት ወንድማቸው ደጅ አዝማች ክንፉ በ1839 ዓ. ም.

[7]"በቆየው የኢትዮጵያ ፊውዳላዊ ባህል ሸፍታ ሆኖ ዱር የሚገባ ሌብነትና ቅሚያ ያማረው አልነበረም፡፡ ሸፍትነት የጨዋ ልጅ ማኩረፊያ ስለ ነበር ጫካ የሚገባው አብዛኛውን ጊዜ የሚፈልገውን ወይም የሚገባውን ሹመትና ጉልት አለማግኘቱን የሚገልጽበት ዘዴ ነበር፡፡ ዕድሜውና ሰውነቱ ለመሸፈት ያልፈቀዱለት የጨዋ ልጅ ደግሞ ከመለመንና ከመመንኮስ ሌላ አማራጭ አልነበረውም፡፡"

"በዚሁ ባህል መሠረት ልሸፍት ብሎ የሚነሳ የጨዋ ልጅ የሚደብቁትና የሚያበሉት ዘመዶች ሲኖሩት ሲሆን የሚሸፍተው፣ በተወለደበትና ባደገበት ዘመዶቹ በሚኖሩበት አገር ነበር፡፡ ካሳና ተዋበች ከተጋቡ በኋላ ሚስትየዋ ባላቸው እንዲሸፍቱ ሲፈልጉ፣ "አገር የለህምን ታጠቅ እንሂድ" ነበር ያሏቸው፡፡ ካሳም፣ "ምነው የለኝ" ብለው ነበር ተያይዘው ቋራ የገቡት፡፡"

በመሞታቸው፣ ወንድሞቻቸውና (አጎታቸው የሚሉም አሉ) ዘመዶቻቸው ይተዳደሩባቸው የነበሩትን የቋራ ጉልቶቻቸውን ራስ ዓሊ ለእናታቸው ለእቴጌ መነን መስጠታቸው ችግር ስለአስከተለባቸውና ስለአስከፋቸው ነው (መርዕድ፣ 1990)። ይኸ የልጅ/የደጅ አዝማች ካሣ ድርጊት ከታሪካዊ ዐውዱ አንጻር ሲመረመር እንደሚከተለው ኾኖ እናገኘዋለን።

የሙገሳ ግጥሙ የሚገልጸውም ጎንደር ቤተ መንግሥት ተቀምጠው የደምቢያና የቋራ ምስለኔዎቻቸውን እያዘዙ ግብር በማሰብሰብ ይኖሩ በነበሩት እቴጌ መነን ላይ ማመጻቸውን አልታዘዝም ማለታቸውን ነው። ከታሪካዊ ዐውዱ መረዳት እንደሚቻለው በግዛታቸው በቋራ ያሉ ኹሉም አሽከሮቻቸውና ምስለኔዎቻቸው ለእቴጌ መነን እየታዘዙ ግብር መሰብሰባቸውን ያሰናከሉባቸው ልጅ ካሣ ናቸው። "ባለቤቱን ካልናቁ፣ አጥሩን አይነቀንቁ" እንደሚባለው ልጅ ካሣ በቋራ ሸፍተው በእቴጌ መነን ተወካዮች ላይ ጥቃት መፈጸማቸው ለእሳቸው አክብሮት መንሣታቸውንና ንቀታቸውን ይገልጻል። ጎንደር ቤተ መንግሥት ተቀምጠው በግዛታቸው ምስለኔዎችን ሾመው ያዙ የነበሩትን እቴጌ መነንን መቃወም ትልቅ ድፍረት ነው ። ድፍረታቸው በሰሜን፣ በጎጃም፣ በዳሞት፣ በወረሂመኑና በላስታ የነበሩትን ደጅ አዝማቾች የሚያስገብሩትን የእቴጌ መነንን ልጅ ራስ ዓሊንም ይመለከታል። የተከበሩትን እቴጌ መነንን አለማክበራቸው፣ በእሳቸው ላይ ማመጻቸው ደፋር፤ ጀግና ለመባልና ለመሞገስ አስችሏቸዋል። ማንፈራጠጣቸውም በመጀመሪያው የሽፍትነት ጊዜያቸው የእቴጌ መነንን አሽከሮችና ምስለኔዎቻቸውን አባርረው ግዛታቸውን መንጠቃቸውንና ሰፊ ቦታ መያዛቸውን ይገልጻል።

ግብር መሰብሰብ ያቃታቸው እቴጌ መነን ከልጅ ካሣ ጋር ታርቀው የልጃቸውን ልጅ ተዋበችን ዳሩላቸው፤ በቋራ ላይም ምስለኔአቸው አድርገው ሾሟቸው። ራስ ዓሊም ለልጅ ካሣ የደጃዝማችነት[8] ማዕረግ ሰጧቸው (መርዕድ፣ 1990)። በምስለኔነታቸው ከፍተኛ ግብር ቢሰበስቡላቸውም እቴጌ መነን እምነት ስለአልጣሉባቸው መቀመጫቸውን ጎንደር አድርገው ቋራን ማስተዳደራቸውን እንዲቀጥሉ ያደርጋሉ። "ካሣ በበኩላቸው የሴት ሕዱግና (የበታች) ምስለኔ በመሆናቸው አልተደሰቱም። ሆኖም ባመቱ እንዲሸፍቱ ያደረጋቸው ነገር ጥርት ብሎ አልታወቀም። እንደ አለቃ ዘነብ አገላለጽ ከኾነ ጉልት ሳይሰጣቸው ጎንደር ውስጥ ከተከታዮቻቸው ጋር ደጅ ጠኚ መስለው በመቀመጣቸው ይመስላል። "በሁለተኛው ዓመት ልጅ ካሣ እጅግ ተቸገሩ ሰዋቸውም ተራበ። እጅግ በደልና መዋረድ ንቀት በመጣባቸው ጊዜ" ይላሉ" (መርዕድ፣ 1990፤ 88)። ልጅ ካሣ ባጋጠሟቸው ችግሮችና "በቤተ መንግሥት ክብር አልተሰጠኝም" በማለት ከጎንደር ቤተ መንግሥት ሸሽተውና ርቀው ወደ ቋራ ወርደው ለኹለተኛ ጊዜ ሸፈቱ። የልጅ ልጃቸው ባል ለመታዘዝ ፈቃደኛ አለመኾን "እምቢ"፣ "አሻፈረኝ" ማለት

"...ሹመት አነሰኝ ጉልቴን ተቀማሁ ብሎ ለሸፈተው የጨዋ ልጅ ግን ይህ የማኩረ ፊያ ዘዴ ዝናን ያተርፍለታል፣ ጎበዝ ያሰኘዋል፣ ኮረዳዎች ጉሮ ወሸባዬ እያሉ ይዘፍኑለታል። ወደ በለጠ ሹመትም ያሸጋግረዋል። የኢትዮጵያ መኳንንት ሁሉ፣ አሁን ስማቸው በየታሪክ መጽሐፉ ጎልቶ የሚነሳው ሰዎች ሁሉ፣ ገናናነታቸውን ያገኙት በመንገዳቸው የወገኖቻቸውን ሬሳ እያነጠፉና እየረገጡ ነበር።" (መርዕድ፣ 1990፤ 85፣ 86)።

[8] አለቃ ዘነብ እንደሚሉት ራስ ዓሊ እናታቸውን ለማስለቀቅ ከልጅ ካሣ ጋር ተደራድረው በደጅ አዝማችነት ማዕረግ ከፍርቃ በመለስ፣ ከዳሞት በመለስ አርማጭሆንም፣ ቋራንም ጨምረው በመስጠት ታረቁ፤ እናታቸውን አስፈቱ። ስለኾነም ልጅ ካሣ ደጅ አዝማች የተባሉት ከዚኽ እርቅ በኋላ መኾኑን እናነባለን (ሊትማን፣ 1902)።

ያስቆጣቸው እቴጌ መነን በወታደር ኀይል ለማንበርከክ ወሰኑ። በፊታውራሪ ወንድይራድ የተመራ ጦር አዘመቱባቸው። ልጅ ካሣ የዘመተባቸውን ጦር ድል አደረጉ። የጦር መሪውን ፊታውራሪ ወንድይራድን ማርከው የአፍ እልፊት መናገራቸውን ኮሶ አስጠጥተው በማግደል ተበቀሏቸው። “ዳግመኛም በኅዳር አስራ ሁለት ቀን ወይዘሮ መነን ጦር ሰደዱባቸው። ልጅ ካሣም ጣቁሳ ሰቀላ ወርካ ላይ በገጠሙት ጊዜ ድል ነሱት”(ሊትማን፣ 1902፤ 12-13)። ልጅ ካሣ ኀይሉን በወታደር ኀይል ለማንበርከክ በተደጋጋሚ ጦር አዝምተው ያልተሳካላቸው እቴጌ መነን ራሳቸው ለመዝመት ይወስናሉ። በሰኔ ወር ፯ ባለ ነጋሪት [፯ ደጅ አዝማች] ጦር መርተው ልጅ ካሣ አሉበት ወደተባለው ቦታ ዘመቱ። እቴጌ መነን ፯ቱን ደጃዝማቾች ያዘመቱት አዝዘው ሳይኾን በልጃቸው በራስ ዓሊ አሳዝዘው ነበር። ልጅ ካሣም ሎሃ እሚባል ቦታ ላይ ጠብቀው ገጠሟቸው። ድል አድርገውም እቴጌ መነንንም ማረኳቸው። የእናታቸውን መማረክ የሰሙት ራስ ዓሊ እናታቸውን እንዲፈቱላቸው ከልጅ ካሣ ጋር ተደራድረው “ከፍርቃ በመለስ አርማጭሆንም ሁሉ ቋራንም ሁሉ ሰጥቼሃለሁ ባሏቸው ጊዜ እናታቸውን ፈትተው ሰደዱላቸው”(ሊትማን፣ 1902፤ 13) ።[9]

እቴጌ መነን ያዘመቱባቸውን ጦር ልጅ ካሣ ድል በማድረጋቸው በአዝማሪ አብተው[10] እንደሚከተለው ተሞግሰዋል።

ሰባቱ ደጅ አዝማች ስምንተኛው ካሣ፣
ምርት አደረጋቸው ወቅቷቸው ተነሣ። (ገሪማ፣ 1996፤ 105)

በማለት ነበር። የተጠቀሰው የሙገሳ ግጥም የተዜመበት ታሪካዊ ዐውድ ከላይ ከተገለጸው ታሪካዊ ኹኔታ በተለየ ምክንያት እንደ ነበር ዊዳሌ ዘግበዋል። ዊዳሌ እንደሚሉት ራስ ዓሊ የእናታቸውን በደጅ አዝማች ካሣ መሸነፍ እንደሰሙ በመጀመሪያ ደጅ አዝማች ጎሹን አዘመቱ። ደጅ አዝማች ጎሹ ጉር አምባ ላይ ከደጅ አዝማች ካሣ ገጥመው ተሸነፉ፤ በጦርነቱም ሞቱ። “ከዚህ በኋላ ራስ ዓሊ በሁዳዴ ጦም ጎጃም ሁነው ፬ ደጃች [ደጅ አዝማች] ያዘው፣ በለው፣ አቤ የላስታውን ብሩ ዓሊጋዝ ደጃች ውቤም ከስሜን ፫ አምበል[11] ጨምረው ሰደዱ። ደጃች ካሳም

[9]ጣቁሳ ላይ በተደረገው ውጊያ ራስ ዓሊ ደጅ አዝማች ውቤን፣ ደጅ አዝማች ብሩ አሊጋዝንና ሌሎች ሦስት ደጅ አዝማቾችን ጦር እንዲልኩ ማዘዛቸውን Shiferaw (1990) ገልጸዋል።

[10]በገሪማ (1996) የተመዘገቡት የሙገሳ ግጥሞች አብተው በተባለው የዐፄ ቴዎድሮስ አዝማሪ የተደረደሩ መኾኑን ይገልጻሉ። ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ተለያዩ ቦታዎች ባደረጓቸው ዘመቻዎች ኹሉ አዝማሪ አብተው አብሮ መዝመቱን ገሪማ ከገለጹት መረዳት ይቻላል። ይኹን እንጂ የዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕሎች ጸሓፊዎችም ኾኑ ሌሎች ሰዎች ለዐፄ ቴዎድሮስ የተደረደሩ የሙገሳ ግጥሞች በአዝማሪ መዜማቸውን እንጂ የአዝማሪውን ስም አልገለጹም።

[11]አምበል (አንበል) የሚለው ስም የጦር መሪ፣ አለቃ፣ አዛዥ፣ አዝማች ማለት ነው። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ዘምተው በነበረበት ጊዜ በአንደኛው ቀን “ሰውን መቁጠር ጀመሩ፤ የሺ አለቃ። የመቶ አለቃ። የአምሳ አለቃ። ያሥር አለቃ። እያደረጉ ሾሙ። የሺውን አለቃ አምበል አሉት ስሙን።” (ሊትማን፣ 1902፤ 24-25) በማለት ተገልጿል። ከዚኽም አምበል የሚለው ወታደራዊ ማዕረግ የሺ አለቃ ማለት መኾኑን እንረዳለን። አምበል የሚለው መጠሪያ ደጅ አዝማች ካሣን እንዲወጉ ከደጅ አዝማች ውቤ ጋር እንዲዘምቱ የታዘዙትንና የዘመቱትን በስም ያልተገለጹትን የጦር መሪዎች በወል ይጠራል። ይኹን እንጂ፣ በእቴጌ መነን መሪነት ደጅ አዝማች ካሣን ለመውጋት በሰኔ ወር የዘመቱት ደጅ አዝማቾች ብዛት ሰባት እንደ ነበር በሊትማን (1902፤ 13) በተዘገበበት አምበል የሚለው ቃል ዐውዳዊ ፍቺ የደጅ አዝማችነት ማዕረግ ያላቸው የጦር መሪዎች ማለትን እንደሚገልጽ መረዳት አልተቻለም። በደጅ አዝማች ውቤ ግዛት ሥር ሌላ ደጅ አዝማች መኖሩን የሚገልጽ ማስረጃም የለም።

እነሂን ሁሉ ተቀብለው ፺ቱንም ፈጁዋቸው፡፡” (ዊዳሌ፣ 1904፤ 3)፡፡[12] ደጅ አዝማች ካሣን በአዝማሪ አብተው ያስሞገሳቸው በስም በተጠቀሱት ደጅ አዝማቾችና በስም ባልተጠቀሱት ፯ አምበል የተመራውን ጦር ድል በማድረጋቸው ነው፡፡

በሰባት ደጅ አዝማቾች የተመራውን ጦር ልጅ ካሣ ማሸነፋቸውን አዝማሪ አብተው በሙገሳ ግጥሙ የገለጸው በንጽጽር ነው፡፡ ንጽጽሩም ትልቅ የእኽል ክምር በአንድ ዐውድማ በአንድ ገበሬ እንደሚወቃው ኹሉ፣ የሰባቱ ደጃዝማቾች ጦር በአንድ ደጅ አዝማች ካሣ ጦር በአንድ የጦር ሜዳ ድል ተደረገ ከሚለው ጋር ነው፡፡ “ምርት አደረጋቸው ወቅቷቸው ተነሣ” የሚለው ሥንኝም ድሉ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ የተገኘ መኾኑን ይገልጻል፡፡ “ምርት አደረጋቸው” የሚለው ለዋጪ ዘይቤ በደጅ አዝማች ካሣ ጦር የተገደሉትን የሰባቱን ደጅ አዝማቾች ነፍጥ አንጋቾች ብዛትና በአንድ ውሱን ቦታ አስከሬናቸው መከመሩን ይነግራል፡፡ “ወቃቸው” የሚለውም በኀይል መመታታቸውን፣ መደብደባቸውንና መጠቃታቸውን ይገልጻል፡፡ ዐውድማ ላይ የሚወቃ እኽል በበሬ እንደሚረገጠው ወይም በበትር እንደሚደበደበው ኹሉ፣ የተሸናፊዎቹ ሰባት ደጅ አዝማቾች ነፍጠኞች ተጠቂና የሚደርስባቸውን ከባድ ጥቃት የማይከላከሉ፣ የደጅ አዝማች ካሣን ጦር መመከት የማይችሉ መኾናቸውን ሙገሳ ግጥሙ ይገልጻል፡፡ “ወቅቷቸው ተነሣ” የሚለው ሐረግም የደጅ አዝማች ካሣን ጦር አሸናፊነት የጠላቶቹን ተሸናፊነትና ለከባድ ጉዳት መጋለጣቸውን ይገልጻል፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ጠላቶቹን ማጥቃቱን ያቆመው ተሸናፊነታቸውን በማረጋገጡ ነው ማለትን ይገልጻል፡፡

ደጅ አዝማች ካሣ ማንፈራጠጣቸው በቀላሉ ተገፍተው የማይወድቁ፣ የማይማረኩ፣ የማይሸነፉ፣ የማይያዙ መኾናቸውን በተግባር አሳዩ፡፡ ማንፈራጠጣቸውም ሰፊ ቦታ ይዘው ኀይላቸውን አደርጅተውና ለጦርነት ተዘጋጅተው የመጠበቃቸው ተምሳሌት ነው፡፡ ከታሪካዊ ዐውዱ እንደተረዳነው በእቴጌ መነን ላይ ያሳዩት እምቢተኝነትም በደጅ አዝማች ካሣ አሸናፊነት ተደመደመ፡፡ ከዚኽ በኋላ የተደረገው ፍጥጫ በእቴጌ መነንና በደጅ አዝማች ካሣ መካከል መኾኑ ቀረ፡፡ ደጅ አዝማች ካሣን እንዲመቱላቸው ባዘጋጁቸው አባትና ልጅ (ደጅ አዝማች ጎሹ ዘውዴና በልጃቸው በብሩ ጎሹ) እና በደጅ አዝማች ካሣ መካከል ኾነ፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ለሦስተኛ ጊዜ አምጸው የዘመቱባቸውን ደጅ አዝማች ጎሹ ብሩን ድል አድርገው በራስ ዓሊ ላይ ዘመቱ፤ ድልም አደረጓቸው፡፡ የካሣ ማንፈራጠጥ ከእቴጌ መነን አልፎ በሌሎችም ላይ ተተገበረ፡፡ ምንም እንኳን የደጅ አዝማች ካሣ አሸናፊነትና ጀግንነት ቢናኝም፣ በዘመኑ የበላይነት የነበራቸውን ራስ ዓሊን ከላያቸው አስቀምጠው ዓላማቸውን እንደማያሳኩ የተገነዘቡት ደጅ አዝማች ካሣ ፊታቸውን ወደ ራስ ዓሊ አዞሩ፡፡ ራስ ዓሊን ለመውጋት ወስነው የዛቻ ቃል ላኩባቸው፡፡ ተቀናቃኞቹን ድል በማድረግ የሥነ ልቦና መነቃቃት የነበረውን ጦራቸውን ይዘው ራስ ዓሊ ወደሚገኙበት ወደ ጎጃም ዘመቱ፡፡ በደጅ አዝማች ካሣ ድርጊት “እንዴት ተደፈርኹ” ማለት ያልቻሉት ራስ ዓሊ ከሰዎቻቸው ጋር መከሩ፤ ጦርነት ለመግጠምም ወሰኑ፡፡ የፍልሚያ ሜዳቸውን አይሻል ላይ

[12]ባሕሩ (፪ሺህ፤ 29) በበኩላቸው ደጅ አዝማች ጎሹ ከተሸነፉ ዐምስት ወር በኋላ“ በሚያዝያ 5 ቀን ደግሞ ካሣ አራት የራስ ዓሊን ደጃዝማቾች “ጎርጎራ ብቸኝ” በተባለ ጦር ሜዳ ላይ አሸነፈ፡፡ ከእነዚህ ሁለቱ እዚያው ጦር ሜዳው ላይ ሞቱ፡፡” በማለት የገለጹት ነው፡፡ ባሕሩ የገለጹት በሊትማን (1902፤ 15) የተመዘገበ ነው፡፡

አደረጉ፡፡ ሰኔ 23 ቀን 1846 ዓ. ም. አይሻል ሜዳ[13] ላይ ባካኼዱት ጦርነት ድሉ የደጅ አዝማች ካሣ ኾነ፡፡ ተሸናፊዉ ራስ ዓሊ ሸሹ፡፡ የራስ ዓሊ የበላይነት አከተመ (Girma, 2014; ባሕሩ፣ ፪ሺ፱)፡፡ የደጅ አዝማች ካሣ ጀግንነትና የበላይነት የማሳረጊያ ምዕራፍ ተከፈተ፡፡ አይሻልና ከዚያም በፊት ባገኙት ድል አዝማሪ አብተው እንደሚከተለው አሞገሳቸው፡፡

> ዓሊን አይሻል ላይ ጎሹንም ጎርጎራ፤
> ታግሎ የጣላቸው ሁሉንም በየተራ
> ለኢትዮጵያ ቢሆን ነው ከአምላክ ባላደራ፡፡ (ገሪማ፣ 1996፤ 57)

የሙገሳ ግጥሙ ደጅ አዝማች ካሣ ድል ካደረጓቸው መሳፍንት መካከል ኹለቱን ይጠራል፡፡ ከታሪካዊ ዐውዱ መረዳት እንደሚቻለው በሙገሳ ግጥሙ በስም ከተጠሩት መሳፍንት በፊት ደጅ አዝማች ካሣ መጀመሪያ በእቴጌ መነን የታዘዘውን በፊታውራሪ ወንድይራድ የተመራውን፣ በኋላም በራሳቸው በእቴጌ መነን መሪነት የዘመተባቸውን ጦር አሸንፈዋል፡፡ እነዚኽ ድሎች በሙገሳ ግጥሙ አለመገለጻቸው ደጅ አዝማች ካሣ ለሥልጣን ለሚያደርጉት ጉዞ ክብደት ላለመስጠቱ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ ለድሎቹ በአዝማሪ አብተውም ትኩረት ያልተሰጣቸው በሙገሳ ግጥሙ ከተገለጹት ድሎች ጋር አለመመጣጠናቸውንና ኅብረተሰቡ ለቀደሙት ድሎች የሰጣቸው ቦታ ዝቅተኛ መኾኑን ይገልጻል፡፡ በራስ ዓሊና በደጅ አዝማች ጎሹ ላይ ያገኟቸው ድሎች ደጅ አዝማች ካሣ ለሥልጣን በሚያደርጉት ጉዞ ወሳኚ ነበሩ፡፡ በሙገሳ ግጥሙ ከተጠቀሱት ድሎች የሚቀድመው ጎርጎራ [ጉር ዐምባ] ላይ ደጅ አዝማች ጎሹን ያሸነፉበት ጦርነት ነው፡፡ አዝማሪ አብተው ደጅ አዝማች ካሣ ቀድመው ጉር ዐምባ ላይ ደጅ አዝማች ጎሹን በማሸነፍ ያገኙትን ድል አይሻል ላይ ራስ ዓሊን ወግተው ካገኙት ድል ጋር እኩል ክብደት አለመስጠቱን ያስገነዝባል፡፡ ራስ ዓሊን ድል ማድረጋቸው ለደጅ አዝማች ካሣ የትግልና የአሸናፊነት ርምጃ ምን ትርጉም እንደነበረው ያስገነዝባል፡፡ ይኽንንም ዜና መዋዕል ጸሐፊው አለቃ ዘነብ አይሻል ላይ ደጅ አዝማች ካሣ ራስ ዓሊን ድል ማድረጋቸው ዘመነ መሳፍንትን በበላይነት የመሩት ኦሮሞዎች በቤጌምድር፣ በጎጃም፣ በላስታ፣ በየጁ፣ በወሎ በሰሜንና በትግራይ የነበራቸው የበላይነት ማክተሙን ገልጸዋል (ሊትማን፣ 1902፤15)፡፡

"ለኢትዮጵያ ቢሆን ነው ከአምላክ ባላደራ" የሚለው ሥንኝ ደጅ አዝማች ካሣ ከእሳቸው የበለጠ ጉልበት የነበራቸውን መሳፍንት ያሸነፉት፣ በፈቃደ እግዚአብሔር ነው፡፡ ኢትዮጵያን ከመሳፍንቱ ጥፋት እንዲታደጉ፣ ሕዝቡን እንዲጠብቁ አምላክ ፈቅዶ ስለላካቸው ነው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ

[13]አይሻል ሜዳ ከደብረ ማርቆስ ከተማ በስተ ምሥራቅ በሙጋና በበጨት ወንዞች መካከል የሚገኝ ሜዳ ነው ( ግርማ (Girma), 2014፡ 295)፡፡
ሊትማን (1902፤ 15) እና ዊዳሌ (1897፤ 4) እንደሚሉት በደጅ አዝማች ካሣና በራስ ዓሊ መካከል የተደረገው ጦርነት የተካኼደው ጎጃም ውስጥ ልዩ ስሙ አይሻል በተባለ ቦታ ነው፡፡ ኹለቱ ዜና መዋዕል ጸሐፊዎች አንደሚሉት ደጅ አዝማች ካሣ ጦራቸውን ይዘው ራስ ዓሊ ወደ አሉበት ወደ ጎጃም በመኼድ የተካኼደ ነው፡፡ ፉሴላ (1958፡ 78) በበኩላቸው ደጅ አዝማች ካሣና ራስ ዓሊ የተዋጉት ደብረ ታቦር ጃንሜዳ ላይ ነው፡፡ ጦርነቱ የተካኼደው ደጅ አዝማች (ፉሴላ ልጅ ይሏቸዋል) ካሣ ጦራቸውን ይዘው በአሞራ ገደል አድርገው ወደ ጠጉር ሚካኤል ከዚያም ወደ ጃንሜዳ በመኼድ ነው፡፡ ይኽ ፉሴላ ዘገባ ከአይሻል በፊት "በግንቦት ደብረ ታቦር ከተደረገው መጠነኛ ውጊያ ጋር በማምታታቸው" መኾኑን መርዕድ (1990፤ 90) ገልጸዋል፡፡

በፈቃደ እግዚአብሔር ተመርተው ለጠላቶቻቸው እሳትና ስለት፣ ለወዳጆቻቸው ደግሞ፣ ሹመትና ሽልማት ሰጡ፡፡ ይኽን ያደረጉት አምላክ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እረኛ፣ መሪ፣ አሳዳሪ እንዲኾኑ በመፍቀዱ ነው፡፡ በእሳቸው የተከናወነው ተግባር "ሰው ባለሥልጣን ቢባልም ከራሱ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ሥልጣን ይቀበላል፡፡" (የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1998፤ 64) ከሚለው የክርስትና እምነት አስተምህሮ ጋራ ይጣጣማል፡፡ ይኽም እግዚአብሔር ሥልጣንን፣ ሹመትን ለመረጠው ይሰጣል የሚለውን መንፈሳዊ እምነት ያጠናክራል፡፡ በሙገሳ ግጥሙ ኢትዮጵያ የሚለው ስም የሚጠራው ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሥልጣን በመጡበት ጊዜ ለራስ ዓሊ ይገብሩና ይታዘዙ የነበሩ መሳፍንት ግዛቶችንና የንጉሥ ኀይለ መለኮትን ግዛት[14] ነው፡፡ በእነዚኽ ግዛቶች የሚኖረውን ሕዝብና የግዛቶቹን ዳር ድንበር ከጠላት መጠበቅ ለአደራ ተቀባዩ ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከአምላክ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ገና በልጅነታቸው በቸንከር ገዳም ሲማሩ ደጃች ማሩን ለማጥቃት የዘመተው የራስ ይማም ጦር በገዳሙ ይማሩ ከነበሩት ተማሪዎች ፵፰ቱን ሲሰልብ እሳቸው መትረፋቸው እግዚአብሔር የሚባርካቸው ምድርን ይወርሷታል በማለት ዳዊት በመዝሙር ፴፪ ቁጥር ፳፪ የተናገረውን ዋቢ አድርገው ዘነብ ጽፈዋል (ሊትማን፣ 1902፤ 5)፡፡ በዘነብ እምነት ደጅ አዝማች ካሣ ከልጅነታቸው ጀምሮ፣ ምናልባትም ከዚያም በፊት እግዚአብሔር ለትልቅ ኀላፊነት አጭቷቸዋል፤ መርጧቸዋል፡፡ ልጅ ካሣ በልጅነታቸው ከአደጋ መትረፋቸው ወደ ፊት በፈቃደ እግዚአብሔር የአባቶቻቸውን መሬትና ኀላፊነት ይወርሳሉ የሚለው እምነት እንዲጸና አድርጓል፡፡

ካሣ ትልቅ ሰው እንደሚኾኑ ኢትዮጵያን እንደሚመሩ እንደሚነግሡ መነኩሴ የተናገረውን ትንቢት መስማታቸውና ማወቃቸው ይኾናል፡፡ ትንቢቱም፡- ፩ኛ ከመወለዳቸው በፊት ወይዘሮ አትጠገብ ያረገዙት ወንድ ልጅ መኾኑንና ታላቅ ንጉሥም እንደሚኾን ለአባታቸው ለ"ወልደ ጊዮርጊስ ኀይሉ"[15] መነኩሴ ይነግራቸዋል፡፡ ፪ኛ አንድ መነኩሴ ለደጃች ክንፉ አብሯቸው የሚኖረው የወንድማቸው ልጅ ካሣ ወደፊት እንደሚገዛ፣ የእሳቸው ልጆች ልጅ መኰንንና ልጅ ጋረድ ለሥልጣን እንደማይበቁ መንገሩን፣ ይኽም የመንፈስ ቅናት ያድርባቸውና ልጅ ካሣን መጥላታቸውን በተግባር ይገልጻሉ፡፡[16] ልጅ ካሣም አኵርፈው ከወንድማቸው ቤት ይወጣሉ፡፡ ሰዎች የልጅ ካሣን በአካባቢው መኖር ሳያውቁ ደጃዝማች ክንፉ ወንድማቸውን የተጣሏቸው ልጅ

[14]ይኹን እንጂ፣ የእሳቸው ፍላጎት ከእነዚኽ ግዛቶች የሰፋ እንደ ነበር ለእሳቸው ከተደረደሩት የሙገሳ ግጥሞች እንረዳለን፡፡ ስናርና ምጽዋ በመዝመት ከመሳፍንቱ ከነጠቋቸው ግዛቶች ጋራ አጠቃለው የመምራት ፍላጎት እንደነበራቸው ምኞቶቻቸውን ለማሞገስ የተደረደሩት ግጥሞች ያስረዳሉ፡፡ መሳፍንቱ ይገዟቸው የነበሩትን ግዛቶች (ሸዋ፣ ወረሂመኖ፣ የጁ፣፣ ላስታ፣ ጎጃም፣ ዳሞት፣ አገው ምድር፣ ደምቢያ፣ በጌምድር፣ ሰሜን፣ ትግራይ፣ ሐማሴን) አዝማሪ አብተው ደጅ አዝማች ካሣ ኢትዮጵያን እንዲመሩ፣ እንዲያስተዳድሩ ከአምላክ አደራ ተሰጥተዋል ለማለት ያስቻለው፡:

[15]በፉሴላ (1958) የተመዘገበው የስም አጠራር የአባትን ስም በማስቀደም የልጅን በማስከተል ነው፡፡ ወልደ ጊዮርጊስ የደጅ አዝማች ካሣ አያት ሲኾኑ አባታቸው ደግሞ ኃይሉ ናቸው፡፡ የአባትን ስም በማስቀደም ልጅን መጥራት በመጽሐፉ ተደጋግሞ ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ፣ "ክንፉ ጋረድ" (ፉሴላ, 1958፡ 70) በማለት የጠሩት አባትን በማስቀደም ነው፡፡

[16]የጠሉበትን ምክንያት ባሕሩ (፪ሺህ፤ 27) ደጅ አዝማች ክንፉ "የአባቱ ልጅ ለሆነው ለካሣ ግን ብዙም ፍቅር አያሳየውም ነበር፡፡ የዚህም ምክንያት ክንፉ ካሣን የልጆቹ ጣውንት አድርጎ ስላየው እንደ ነበር ይገመታል፡፡ ክንፉ "የማሩ ቀመስ"ን ለልጆቹ ለማውረስ ለነበረው ጽኑ ፍላጎት ካሣን እንቅፋት ሆኖ ስላየው የሚመለከተው በክፉ ዓይን ነበር፡፡" በማለት ገልጸውታል፡፡

*ካሣ እንጂ ልጆቻቸው እንደማይገዙ መነገራቸውን መስማታቸውን ሲያወሩ ልጅ ካሣ መስማታቸውን ፋሴላ (1958፡ 69,70) ዘግበዋል፡፡ በዚኽ በፋሴላ ከተመዘገበው ትንቢት ጋር በዊዳሌ የተመዘገበው በከፊል ይመሳሰላል፡፡ ትንቢቱም "ደጃች ክንፉ ለማኅበረ ሥላሴ መነኮሳት ከልጆቼ አልጋዬ እንዳይሄድ እዘኑልኝ አትርሱኝ ብለው ፪ ሰዎች ላኩ እነዚያም መነኮሳት ከልጆችህ አልጋህን የሚይዝ የለም ገዢው የወንድምህ ልጅ ካሳ ነውና አደራ ብለህ ንገረው ብለው ላኩባቸወ[ው]" (ዊዳሌ፣1904፤ 1) በማለት ተመዝግቧል፡፡*[17]

*ይኽ ትንቢት ልጅ ካሣ ላደረጓቸው እንቅስቃሴዎች ስንቅ እንደኾናቸው ይታመናል፡፡ በደጅ አዝማች ጎሹ ቤት በቆዩባቸው ጥቂት ዓመታት የተመሰገኑበትን የጀግንነት ተግባር ለመፈጸም ከተፈጥሯዊ ባሕርያቸው በተጨማሪ የነገ ሕልማቸው ብርታትንና ድፈረትን እንደ ሰጣቸው ይታመናል፡፡ በአንደበታቸው ሀገር መግዛትና ሕዝብ መምራት የሚችሉት በአምላካቸው ፈቃድ መኾኑን መናገራቸው ስለእሳቸው የተነገረውን ትንቢት በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ መንገድ መስማታቸውን ይጠቁማል፡፡ ከደጅ አዝማች ጎሹ ሸሽተው ወደ ቋራ ወርደው "እኔም ባገኝ እናንተም ብታገኙ አንድነት ሁነን እንድንበላ" በማለት ከሽፍቶች ጋር ከተስማሙ በኋላ ሽፍቶች ቃላቸውን በማፍረሳቸው የተቆጡት ልጅ ካሣ ፲፪ ራሳቸውን ኾነው ፸ዎቹን ሽፍቶች ገጥመው ድል ያደርጓቸዋል፡፡ ይኽንን ያደረጉት በእግዚአብሔር ኀይል መኾኑን ዜና መዋዕል ጸሓፊያቸው ዘነብ ገልጸዋል፡፡ በማረኳቸው ፯ ሽፍቶች ላይ ቅጣት መፈጸማቸው ተገቢ አለመኾኑን ወሰን ይልማ የተባሉ ሰው ሲነቅፏቸው ልጅ ካሣ "እግዚአብሔር ቢሰጠኝ እገዛለሁ፡፡ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምን የሚሆን አለ" (ሊትማን፣ 1902፤ 7) በማለት መመለሳቸው የትንቢት ተስፋ በውስጣቸው ለማደሩ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ "የንቀት ድርጊት ተፈጽሞብኛል" ብለውና አኩርፈው ከጎንደር ቤተ መንግሥት ወደ ቋራ ሲወርዱ በደምቢያ ለነበረው የእቴጌ መነን ወታደር "የወደድኸኝ ተከተለኝ የጠላኸኝ አገሬን ልቀቅ"፣ ይደግፈኛል ላሉት ሕዝብ ደግሞ፣ "በክርስቶስ ኀይል መጥቸልሃለኹ" በማለት ዐዋጅ ያስነገሩት፣ በፊታቸው የተገኘውን የእቴጌ መነን ወታደር ነፍጡንና መሣሪያውን ያስገፈፉት (ፋሴላ፣1958፤ 74) ስለ እሳቸው ቀድሞ የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም በማሰባቸው ነው፡፡*

*በእቴጌ መነን የተላከባቸው ጦር ቋራ መድረሱን እንዳወቁ ልጅ ካሣ "...ወደ ዱር ገብተው ጸሎት ሲያደርጉ በጉልበታቸው ተምበርክከው [እንዳሉ] ከዛፉ ወርዳ ርግብ ተቀመጠችባቸው ይባላል፤ እርሳቸው ተነሥተው ምስጋና ይኹን ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ብለው ፊታቸውን ፫ ጊዜ አማትበው ወደ ምድር ፫ ጊዜ ሰገዱ እና፡፡ <u>እንግዲህ ንግርቴ ደረሰ</u> ብለው ወደ ሰልፋቸው ተመለሱ" (ፋሴላ፣ 1958፤ 75) (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡ ስለኾነም በሙገሳ ግጥሙ ደጅ አዝማች ካሣ ኢትዮጵያን እንዲመሩ ከአምላክ የተላኩ መኾናቸው የተነገረው በኅብረተሰቡ ውስጥ ይወራ*

---

*[17]ፋሴላ ለደጅ አዝማች ክንፉ አንድ መነኩሴ ወደ ቤታቸው በመኼድ ትንቢቱን እንደነገራቸው ሲገለጽ በዊዳሌ ደግሞ የማኅበረ ሥላሴ መነኮሳት ናቸው፡፡ ልጅ ካሣ የደጅ አዝማች ክንፉ ወንድም፣ በዊዳሌ ደግሞ የወንድም ልጅ መኾናቸው ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም በፋሴላ ልጅ ካሣ ወደ ደጅ አዝማች ጎሹ የኼዱት ከደጅ አዝማች ክንፉ በመጣላታቸው ምክንያት ከድተው እንደኾነ ተገልጿል፡፡ ዊዳሌ ግን "ወታደርነት ከደጃች ጎሹ ሄዱ" የሚል እንጂ የኼዱበትን ምክንያት አይገልጽም፡፡*

የነበረውንና በደጅ አዝማች ካሣ ይታመንበት የነበረውን ትንቢት መሠረት ያደረገ ነው ማለት ነው፡፡

በፍካሬ ኢየሱስ የተነገረው ትንቢት በሳቸው እንደሚፈጸም በማመናቸውና መመሪያቸው በማድረጋቸው ወደ ሥልጣን የሚያደርጉትን ጉዞ አጠናከረው ቀጠሉ፡፡ በመርዕድ (1990፤ 91) በተጠቀሰው የፍካሬ ኢየሱስ ትንቢት፡- "ከምሥራቅ በኩል ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ አስነሳለሁ እሱም ፈቃዴን የፈጸሙትን ከመከራ ያተረፍኳቸውን የሚሰበስብ ነው፡፡ ጳጳስም ይወጣል ምድርን የሚባርክ ሰውን ደስ የሚያሰኝ፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ይታደሳሉ፡፡ በዚያ ዘመን ጥል፣ ክርክር፣ ሐሰት ነገር የለም፤ ሁሉም በንጉሥ ቃል ይጸናል፤ ምድርም በጳጳስ ቃል ትባረካለች፤ ስሜም ይከበራል፡፡ ፍቅር፣ በረከት በምድር ላይ እንደ እህል ይዘራል፡፡ ፍቅር ሰላምና ደስታ እንጂ ፀብ፣ ክርክር የለም፡፡" የሚል ነው፡፡ ይኸንን ትንቢት እየሰሙ ያደጉት ካሣ ድል እየቀናቸው ሲኼድ ራሳቸውን የትንቢቱ ፈጻሚ አድርገው አመኑ፡፡ የእሳቸውን እምነት ሌሎችም ተጋሩት፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ሕዝቡን እንዲጠብቁ አደራ እንደተሰጡ የተገለጸው የኢትዮጵያ ሕዝብ "ድሀ ተበደለ ፍርድ ቀጠነ" ብሎ የሚጠብቀው መሪ፣ አስተዳዳሪ የሚያስፈልገው ነበር፡፡ የዘመነ መሳፍንት ቁንጮ የነበሩት ራስ ዓሊና ዘመዶቻቸው በሕዝብ ላይ ይፈጽሙት የነበረውን ግፍ አምላክ ተመልክቶ ቴዎድሮስን እንዳስነሣ የንጉሡ ዜና መዋዕል ጸሓፊ አለቃ ዘነብ እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡ "ዘመዶቻቸውም [የራስ ዓሊ ዘመዶች] እጅግ ድኃ በበደሉ ጊዜ የአበሻ ሰዎች ሁሉ ፍርድን ፡፡ መልካም መስራትን፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት በተው ጊዜ፡፡ በስም ክርስቲያን ተብለው፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ፈንታ አስማት፡፡ ምንዝር ስካር ቧልት ጥመት ባደረጉ ጊዜ፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ቀናዒ ነውና፡፡ ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሣ ሁሉን የሚቀጣ፡፡" (ሊትማን፣ 1902፤ 3)፡፡[18] "ኹሉን የሚቀጣ" የሚለው ሐረግ ሕግንና ሥርዓትን የማያከብርን፣ ሕዝብን የሚበድልን፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን አደራ መወጣት ያልቻለን ሰው ማሰርን፣ ገንዘብ ማስከፈልን፣ በግርፋት ወይም በአካል ወይም በሞት መቅጣትን ይገልጻል፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በጥፋተኛ ላይ ቅጣት የሚበይኑት ወይም የሚወስኑት ሕግንና ሥርዓትን እንዲያስከብሩ፣ የተበደለን እንዲያስክሱ እግዚአብሔር ከሰው ኹሉ መርጦ ሥልጣን ስለሰጣቸው ነው፡፡ በሀገር አውራነታቸውም ሕዝብን ከበደል ይጠብቃሉ፡፡[19] የሕዝብ መሪና አሳዳሪ

[18] ሥርዓተ ነጥቡ ከምንጩ እንደተገኘው ነው፡፡

[19]ዐፄ ቴዎድሮስ ፍትሕ የማስፈን ፍላጎት እንደነበራቸው የሚያስረዱ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- "ደብረ ወርቅ ላይ ደጅ አዝማች ካሳ ሰፍረው ሳሉ ፪ ሰዎች ተካሰሱ፡፡ ከሳሹ ሹምዬ ጃሎ ነው፡፡ ተከሳሹ ጠቦ ወልደ ሚካኤል ነው ስሙ ፡፡ ሹምዬ ጃሎ ለጠቦ ፈረስ ሰጥቶ ኑሩዋል፡፡ ደጃች ካሳ እራስ አሊን ድል ባደረጉ ጊዜ ሹምዬ ከራስ ሆኖ ተገፈፈ ልብስ ባጣ ጊዜ ጠቦን ፩ ብር ለልብሴ ተባክህ [እባክህ] ስጠኝ አለው፡፡ ጠቦም አልሰጥም አለ፡፡ ከደጃች ካሳ በደረሱ ጊዜ ወሮታ አለኝ አለው ሹምዬ ጃሎ፡፡ ደጅ አዝማች ካሳም ወይ ሰጠኸኝ ወይ አልሰጠኸኝም በል አሉት፡፡ ሊሸፍጥም ፈለገ፡፡ ደጅ አዝማች ካሳም ተቆጡት፡፡ ጠቦም ፈረስ አልሰጠኸኝም አለ፡፡ ሹምዬም ፈረስ እንደ ሰጠሁህ እግዚአብሔርን ምስክር ልጥራብህ አለ፡፡ ጠቦም የእግዚአብሔርን ምስክርነት ፈራ፡፡ አዎን ፈረስ ሰጥተኸኛል አለ፡፡ ደጅ አዝማች ካሳም እግዚአብሔርን እንደ ፈራ ባዩ ጊዜ ስለ እውነቱ፡፡ እኔ እከፍልልሀለሁ አሉት፡፡ ለከሳሹ ፲ ብር ፩ ፈረስ ፩ በቅሎ ሰጡት፡፡ እውነትን ሰው ሁሉ እንዲማር ብለው፡፡" (ሊትማን፣ 1902፤ 14-16)፡፡ መርዕድም (1990) ይኸንንና ሌሎችን ተግባሮቻቸውን በመግለጽ ለፍትሕ የቆሙ እንደ ነበሩ ገልጸዋል፡፡ ባሕሩ (፪ሺህ) በበኩላቸው "ባሕሪው [የዐፄ ቴዎድሮስ] ደግሞ ለፍትሕና ለእኩልነት መቆርቆር ነበር፡፡" በማለት ገልጸዋል፡፡ ስመ መንግሥታቸውን ቴዎድሮስ ያሉበት ምክንያት አስተዳደር በተበላሸበት፣ ድልወትና ምንዝርና በበዛበት ሰዓት

በመኾናቸውም ለጠላታቸው እሳትንና ስለትን፣ ለወዳጃቸው ሹመትንና ሽልማትን ይሰጣሉ፡፡ ሕዝቡ ፍትሕን ያሰፍናሉ የሚደርስበትን ጥቃት ይታደጋሉ ማለትን ይገልጻል፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን እግዚአብሔር ያስነሣው የሰውን ክፋት ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል እንደኾነ አለቃ ዘነብ ይገልጻሉ፡፡ "ይህነን ሁሉ ክፋት ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በሀበሻ ላይ ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሳ ምንዝር የማይወድ፡፡ ገንዘብ ሐሰት ሥርቆት የማይወድ፡፡ ሽፍጥንም ሁሉ የማይወድ፡፡ እግዚአብሔርን የፈራ፡፡ እጅግ የሚሰጥ፡፡ እንግዳ የወደደ ለታመመ የሚያዝን፡፡ ከአንዲት ሴት[20] የቀረበ፤" (ሊትማን፣ 1902፤ 5)፡፡ ለዐፄ ቴዎድሮስ ክርስቶስ ኀይሉን እንደ ሰጣቸው ሥርግው ገላው (2008፤ 214) "ከአጼ ኢዮአስ[21] ወዲህ ሐበሻ ተዋርዳ የነበረችውን በጉልበትና በስም አኵራት፡፡ ከፍ ከፍ አደረጋት፡፡ ክርስቶስም ውርደትዋን በቃ ሲል ኃይሉን ለአጼ ቴዎድሮስ ሰጠ፡፡ በቀኝ በግራ የነበረውን ሁሉ መሳፍንት እየቀጠቀጠ አስታጠቀው፡፡" በማለት ገልጸውታል፡፡

ድል የቀናቸው ደጅ አዝማች ካሣ ራስ ዓሊን ድል ከመቱ በኋላ ከጎጃም ወደ ደብረ ታቦር ከተማ ገሥገሡ፡፡ የራስ ዓሊ መቀመጫ የነበረችውን ከተማ ከተቆጣጠሩ በኋላ በከተማዋና አካባቢው ለሚገኘው ሕዝብ፣ "...እርስት አለኝ ጉልት አለኝ የምትል የሴት ወይዘሮ የወንድ መኰንን በምን ተነቀልኩ እንዳትል ግባ የአባትህን ሰጥቸሃለሁ፡፡ ከራስ ዓሊ ጋር የሸሸህ ወታደር ምሕረት አድርጌልሀለሁ ግባ፡፡" በማለት ዐዋጅ አስነገሩ፡፡ ክራሞታቸውንም በደብረ ታቦር ከተማ አደረጉ፡፡ "አዋጁን የሰማውና ትእዛዙን የተቀበለው የቤጌምድር፤ የዋድላና የደላንታ ሕዝብ እንዲሁም ከራስ ዓሊ ጋር ሸሽቶ የነበረው ሠራዊት ገባላቸው፡፡" (ገሪማ፣ 1996፤ 61)፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ "ዳግማዊ ቴዎድሮስ" ተብለው ከነገሡ በኋላ መጀመሪያ ወደ ወሎ ቀጥሎም ወደ ሸዋ ዘመቱ፡፡ ኹለቱም ግዛቶች በቀላሉ እጅ ባለመስጠታቸው ለወራት የዘለቀ ፈታኚ ጦርነት ገጥሟቸዋል፡፡ በመጨረሻ ግን ድል አድርገው አስገብረዋቸዋል፡፡ በወሎና በሸዋ እንዲኹም በሌሎች አካባቢዎች ያመጹ መሳፍንትን ረጅም መንገድ እየተጓዙ ማጥቃታቸውን ቀጠሉ፡፡ ድል በማድረጋቸውም በአዝማሪ መሞገሳቸውን በታሪክ ሰነዶች ከተመዘገቡት ቃል ግጥሞች እንገነዘባለን፡፡ ከተሞገሱባቸው ቃል ግጥሞች ጥቂቶቹን በተራ ቁጥር 2. 2 በተገለጸው ንዑስ ርእስ ሥር ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

---

ቴዎድሮስ የተባለ ንጉሥ ተነሥቶ የተበላሸውን አስተዳደር አስወግዶ ሰላምንና ትክክለኛ ፍርድን ያሰፍናል የሚል ትንቢትን ለራሳቸው በማድረጋቸው ነው (ተክለ ጻድቅ፣ 1981፤ መርዕድ፣ 1990)፡፡

[20] ይኸ አገላለጽ ተዋበችን ከማግባታቸው በፊትና ተዋበች ከሞቱ በኋላ የነበራቸውን ሕይወት የሚገልጽ አይደለም፡፡ ልጅ ካሣ በሽፍትነት የሚኖሩትን የአቶ እንግዳ ወርቅን ልጅ አግብተው ይኖሩ ነበር፡፡ ምንትዋብን ያገቡት የእንግዳን ልጅ ፈትተው ነው፡፡ (የልጅ ካሣ ሚስት የነበሩት የአቶ እንግዳ ወርቅ ልጅ ስማቸው ማን ይባል እንደ ነበር፣ በመካከላቸው ልጅ መውለድ አለመውለዳቸውን የተመለከተ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡) ዳግማዊ ዐፄ በቴዎድሮስ በንግሥናቸው ቀን ከተዋበች ጋር ቢቆርቡም እርሳቸው ከሞቱ በኋላ የደጅ አዝማች ውቤን ልጅ ጥሩወርቅን ከማግባታቸውም በላይ ሌላም ቅምጥ እንደ ነበራቸው ተዘግቧል፡፡

[21] በስመ መንግሥታቸው አድያም ሰገድ በመባል የሚታወቁትን የኢዮአስ ቀዳማዊን ዘመነ መንግሥት ይጠቅሳል፡፡ የእሳቸው ሥልጣነ መንግሥትም ከ1747 እስከ 1761 ዓ. ም. ነበር፡፡ ከእሳቸው በኋላ የመጡት ነገሥታት በስም እንጂ ኀይል ኖሯቸው የሚያዙ የሚናዙ አልነበሩም፡፡ ከኢዮአስ በኋላ የነገሡት የነገሥታት ሥልጣን በተለያዩ ቦታዎች በነበሩ መሳፍንት ወሳኚነት ሥር ነበር፡፡ የነገሥታቱ ስም ዝርዝርና የነገሡበት ጊዜ በሥርግው ገላው (2008፤ 92) ተመዝግቧል፡፡

## 2. 2. ዳግማዊ ቴዎድሮስ ተብለው ከነገሡ በኋላ የተደረደሩላቸው ሙገሳዎች ትንተና

በዚኽ ንዑስ ርዕስ ሥር የምንመለከተው ዐፄ ቴዎድሮስ ተብለው ከነገሡ በኋላ የተደረደሩላቸውን የሙገሳ ግጥሞች ነው፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹ ቴዎድሮስ የሚለውን ስም የሚጠሩ ወይም ከንግሥና በኋላ የተከናወኑ ድርጊቶችን የሚገልጹ ናቸው፡፡ አንዳንድ የሙገሳ ግጥሞችም "ታጠቅ" ወይም "አባ ታጠቅ" በሚል ስም በመጥራት ከንግሥና በኋላ የተፈጸመን ተግባር ይገልጻሉ፡፡ ከንግሥና በፊት የልጅ ካሣን መከፋት በተረዱትና በተጋሩት ባለቤታቸው በተዋበች እንዲሸፍቱ የተነገራቸው "ታጠቅ" የሚል የቅስቀሳ ቃል የተስማማቸው ልጅ ካሣ ራሳቸውን ጠርተውበታል፡፡ ከንግሥናቸው በኋላም የፈረስ ስማቸው መጠሪያ አድርገውታል፡፡ በአንዳንድ የሙገሳ ግጥሞችም በዚኽ ስማቸው ተጠርተውበታል፡፡ ስለኾነም ንጉሡን "ታጠቅ ወይም አባ ታጠቅ" በማለት የሚጠሩ የሙገሳ ግጥሞች ከንግሥና በፊት ወይም በኋላ የነበረውን ጊዜ እንደሚጠሩ ለመወሰን ታሪካዊ ድርጊቱ የተከወነበትን በመመርመር ለማስረዳት ጥረት ተደርጓል፡፡

ደጅ አዝማች ካሣ ደብረ ታቦር እያሉ ደጅ አዝማች ውቤ እንዲገቡላቸው ጠየቁ፡፡ ፈቃደኛ ባለ መኾናቸው ደጅ አዝማች ውቤን ለመውጋት "ስሜን ሰሜን እነግርሃለሁ" በማለት በ1847 ዓ. ም. ወደ ስሜን ዘመቱ፡፡ ደጅ አዝማች ውቤንም ድል አደርጉ፡፡ ደጅ አዝማች ውቤን ድል አድርገው የካቲት 5 ቀን 1847 ዓ. ም. ደጅ አዝማች ውቤ ባሳነጺት ደረስጌ ማርያምና ከግብፅ ባስመጧቸው ጳጳስ በአቡነ ሰላማ ቅብዐ መንግሥት ተቀብተው በደረስጌ ማርያም ስመ መንግሥታቸውን "ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" አሰኝተው ነገሡ (ተክለ ጻድቅ፣ 1981)፡፡ በደጅ አዝማች ውቤ ድል መኾን የሕዝቡ ስሜት ምን እንደ ነበር የሚከተለው የአዝማሪ ግጥም ያስረዳል፡፡

> ሰብኣ በጌምድር ወልቃይት ጠገዴ፣ ሰሜን አርማጭኾ፣
> ለጎይለኛው ንጉሥ ተገዛን እንኾ፡፡ (ደስታ፣ 1962፤ 243)

በሙገሳ ግጥሙ የተጠቀሱትን ቦታዎች ይገዙ የነበሩትን ደጅ አዝማች ውቤን ወግተው በማሸነፋቸው ደጅ አዝማች ካሣን በአዝማሪ አስሞግሷቸዋል፡፡ ስሙ ባልተገለጸ አዝማሪ የተዜመው ይኽ ሙገሳ፣ የንጉሡን አሸናፊነትና ከገዢዉ ጋር አብሮ አልገዛም ያለውን ሕዝብ ተሸናፊነት ይገልጻል፡፡ አዝማሪው በግጥሙ የጠራቸው የደጅ አዝማች ውቤ ክፍላተ ግዛትን[22] (ወልቃይትን፣ ጠገዴን፣ ሰሜንንና አርማጭኾን)ና በራስ ዓሊ ምስለኔ ሥር የነበረውን ሰብአ በጌምድር (ኹሉንም የበጌምድር ሕዝብ) ነው፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ በሙገሳ ግጥሙ የተጠቀሱትን

[22]የደጅ አዝማች ውቤ ግዛቶች በገጣሚው የተጠቀሱት ቦታዎች ብቻ አልነበሩም፡፡ የደጅ አዝማች ውቤ ግዛታቸው ወገራን፣ ትግራይን እና ሐማሴንን ይጨምራል፡፡ ራስ ዶሪ በባረኩላቸው በትግራይ የነበሩትን የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውን ተደጋጋሚ ዘመቻዎችን በማድረግ ወግተውና አሸንፈው ደጅ አዝማች ካሣይ ሰባጋዲስን አሸንፈው አስረው ከወገራ እስከ ሐማሴን ያለውን ግዛታቸውን አጽንተዋል (Shiferaw, 1990: 27, 37) በማለት ገልጸዋል፡፡ በመኾኑም የደጅ አዝማች ውቤ ግዛት ደጅ አዝማች ውቤ ከጎንደር ባንብሎ አንስቶ እስከ ቀይ ባሕር ጠረፍ ድረስ ነበር (ገነት፣ 2009፤ 371)፡፡ ደጅ አዝማች ውቤ የትግራይን 44 ነጋሪት ጦር ይዘው ቧሂት ላይ ደጅ አዝማች ካሣን ውጊያ የገጠሙት (ዊዳሌ, 1904: 5) ትግራይ ግዛታቸው ስለ ነበርና በሥራቸው የነበረውን ባለነጋሪት መሳፍንት ከጎናቸው ተሰልፎ እንዲዋጋ ማዘዝ በመቻላቸው ነበር፡፡

ቦታዎች ይገዙ የነበሩትን መሳፍንት ያሸነፉት ንጉሥ ከመባላቸው በፊት ደጅ አዝማች በሚል ማዕረግ ይጠሩ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ አዝማሪው በሙገሳ ግጥም ንጉሥ የሚለውን ስም መጠቀሙ ቴዎድሮስ ተብለው ከነገሡ ከ1847 ዓ. ም. በኋላ ለመኾኑ ማስረጃ ነው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ሥልጣን የመጡበት ወቅት፣ ኢትዮጵያ መሪ በፈለገችበት ጊዜ መኾኑን አዝማሪ አብተው በሚከተለው በሙገሳ ግጥሙ ገልጿል፡፡

ብዙ ጊዜ ኾናት ደህና ባል ካጣች፣
አኹን ግን በታጠቅ[23] ይኸው ታፈረች፡፡ (ገሪማ፣ 1996፤ 57)

አዝማሪው ሙገሳውን ያቀረበው ለዋጭ ዘይቤን በመጠቀም ነው፡፡ ኢትዮጵያን ሚስት፣ ገዢዋን፣ መሪዋንና አስተዳዳሪዋን ደግሞ ባል አድርጎ ይገልጻል፡፡ የሙገሳ ግጥሙ በባልና በሚስት መካከል የሚኖረው ግንኙነት የክርስትና እምነትንና ባህልን መሠረት በማድረግ ሲመረመር የሚከተለውን ሐሳብ ይናገራል፡፡ በክርስትና እምነት "እግዚአብሔርን በመፍራት ለባልንጀሮቻችሁ ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፡፡ ሴቶችም ለጌታችን እንደሚታዘዙ ለባሎቻቸው ይታዘዙ፡፡ ክርስቶስ አካሉ ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ራስዋ፣ አዳኝዋም እንደሆነ ወንድ ለሴት ራስዋ ነውና፡፡ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትታዘዝ እንዲሁም ሴቶች ለባሎቻቸው በሁሉ ይታዘዙ፡፡ ወንዶችም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ራሱንም ስለ እርስዋ ቤዛ አድርጎ እንደ ሰጠላት ሚስቶቻቸውን ይውደዱ" (ኤፌ 5 ፤ 21-26) የሚለውን ሃይማኖታዊ ትእዛዝ ያስታውሳል፡፡ በባህላዊ ግንኙነታቸው "ደህና ባል" የሚለው ሐረግ አርሶና አምርቶ ወይም ነግዶና አትርፎ ሚስቱ እንዳይቸግራት፣ ቤተሰቡ ለከፋ ሕይወት እንዳይጋለጥ ይተጋል፡፡ ከብት አርብቶና ወተት አልቦ ያጠጣል፣ በቅቤ ያበላል፡፡ ሀብቱን፣ ንብረቱን ከነጣቂ ይከላከላል፤ ይጠብቃል፡፡ ተሟግቶ በመርታት ያኮራል፡፡ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚከበርበትን ተግባር ይፈጽማል፡፡ ማንነቷ ያልተገለጸችው ሚስት እነዚኽንና ሌሎችንም የሚጠበቁበትን ኀላፊነቶች የሚወጣ ባል አጥታ ረጅም ጊዜ የኖረችው ሴት የምትወከለው ኢትዮጵያን ነው፡፡ ኢትዮጵያ የሚመራት፣ የሚያስተዳድራትና ጌታዋ የሚኾናት ባል ሳይኖራት ብዙ ጊዜ አሳለፈች[24] የሚለው ኢትዮጵያ መሪ

---

[23]ታጠቅ የሚለውን ቃል ቀድመው የተናገሩት ወይዘሮ ተዋበች የደጅ አዝማች ካሣ ሚስት ናቸው፡፡ ታሪኩም ደጅ አዝማች ካሣ የኮሶ መድኃኒት ጠጥተው "ምሳዬን" ብለው ለእቴጌ መነን ላኩ፡፡ ወይዘሮ መነንም ወርች ሥጋ ላኩላቸው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ የተላከላቸውን የወርች ሥጋ "ለክብሬ አይመጥንም" በማለት አዘኑ፡፡ ማዘናቸውን የተረዱት ተዋበች፣ በባላቸው ላይ በደረሰው ውርድት ተቆርቁረው "ሀገር የለህም? ታጠቅ እንሂድ ይልቅ" አሏቸው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣም ታጥቀው ሚስታቸውን ይዘው አገራቸው ቋራ ገብተው ሸፈቱ፡፡ ብዙ ሎሌ ገባላቸው፡፡ አባ ታጠቅ ተባሉ (ሥርግው ገላው፣ 2008፤ 204-205)፡፡ ታጠቅ የሚለው ቃል ደጅ አዝማች ካሣ ዐፄ ቴዎድሮስ ተብለው ከነገሡ በኋላ የፈረስ ስማቸው ኾነ፡፡

[24]ብዙ ጊዜ የሚለውም የጎንደር ዘመነ መንግሥት ከተዳከመበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ዓመታት ማለትም የኢዮአስ ሥልጣነ መንግሥት ካበቃበት ከ1761 ዓ. ም. ጀምሮ ዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ነገሡበት 1847 ዓ. ም. ያለውን ከ82 ዓመት በላይ ያጠቃልላል፡፡ መርዕድ (1990፤ 77) ዘመነ መሳፍንት ሰማኒያ አራት ዓመታት ሰፍኖ መቆየቱን ሲገልጹ Shiferaw (1990: 25) በበኩላቸው ዘመነ መሳፍንት 1786 እስከ 1853 (እ. አ. አ) እንደዘለቀ ይገልጻሉ፡፡ በዚኽ ስሌት ዘመነ መሳፍንት ዕድሜ 67 ዓመታት ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ ሊትማንም (1902፤ 15) "ንጉሥ በጠፋ በ፳፩ ዘመን እግዚአብሔር ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሣ፡፡" በማለት ዘመነ መሳፍንት ሰፍኖ የቆየበትን ጊዜ ዘግበዋል፡፡ አቻምየለህ (2012፤ 112) በበኩላቸው "ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለዘጠኝ አስርት ዓመታት የቆየውን ዘመነ መሳፍንትን ያቆሙና የተዋህደች ኢትዮጵያ ጅማሬ [ጀማሪ] ናቸው፡፡" በማለት ዘመነ መሳፍንት ሰፍኖ የቆየበትን ጊዜ ይገልጻሉ፡፡ ከዚኽም በኢትዮጵያ ዘመነ መሳፍንት ለምን ያህል ጊዜ ሰፍኖ እንደቆየ በልዩነት እንደሚነገር መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሳይኖራት ያሳለፈችውን ጊዜ ይገልጻል፡፡ ይኸም በዘመነ መሳፍንት የተለያዩ ክፍላተ ሀገርን ይገዙ በነበሩ መሳፍንት የተመራችበትን ጊዜ ይጠራል፡፡ አዝማሪ አብተው በሙገሳው ታጠቅ ሀገርን የመምራት ብቃት ያልነበራቸውን የየአካባቢው ገዢዎች በማስወገድ ኢትዮጵያን ማስተዳደራቸው እንድትታፈርና እንድትከበር አደረጉ፤ ታጠቅን በማግባቷ ተከበረች፤ ታፈረች ማለትን ይገልጻል፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በነገሡበት ዓመት ለማስገበር ዘመቱ፡፡ ዛሬ ሰሜንና ደቡብ ወሎ ተብሎ የሚጠራውን ይገዙ የነበሩትን መሳፍንት ለማስገበር የተራዘመ ዘመቻ አካኼዱ፡፡ ዘመቻው "ኩዳዴና ክረምት ያላገደው ስድስት ወር ያህል የፈጀ ነበር፡፡" (ባሕሩ፣ ፳፫ሺ፣ 29-30፤ ዊዳሴም (1904፣ 13)፡፡ ባሕሩ እንዳሉት በዐመጻቸው የተፈታተኗቸውን እጅና እግር በመቁረጥ መቀጣጫ ካደረጉ በኋላ ጊዜያዊ ድል አገኙ፡፡ ይኹን እንጂ ወሎ ላይ ባገኙት ድል አዝማሪ ያሞገሰበትን ግጥም አላገኘንም፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የወሎ ተቀናቃኞቻቸውን ድል አድርገውና አስገብረው ለተመሳሳይ ተግባር ወደ ሸዋ ዘመቱ፡፡ ወደ ሸዋ ባደረጉት የመጀመሪያው ዘመቻ ወሎ ላይ እንዳጋጠማቸው ያለ ተቃውሞ እንዳላጋጠማቸው Crummey (1971) ቢገልጹም በመጀመሪያው ዘመቻ በግሼ ግንባር የተደረገው ውጊያ ዐምስት ወራት የፈጀ ነበር፡፡ ቀኑን ሙሉ ይካኼድ በነበረው ከባድ ውጊያ የቴዎድሮስ ጦር ቢፈተንም ከወራት በኋላ ድሉ የዐፄ ቴዎድሮስ ኾነ፡፡ ግሼ ላይ ድል ከቀናቸው በኋላ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደፊት ገፍተው የመንዝ፣ የግድምና የኤፍራታ ገዢዎች እጃቸውን እንዲሰጡ አደረጉ፡፡ በሌሎች የሸዋ ግዛት ክፍሎች የሚገኙ የንጉሥ ኀይለ መለኮት ደጋፊዎች ግን ከፍተኛ መከላከል ቢያደርጉም የመሣሪያ ብልጫና የተሻለ ወታደራዊ ሥነ ሥርዓት የነበረው የዐፄ ቴዎድሮስ ጦር አሸነፈ፡፡ በንጉሥ ኀይለ መለኮት ድንገተኛ ሞት የመዋጋት ስሜቱ የቀነሰው የሸዋ ጦር የሥልጣን ወራሺ የነበሩትን ሕፃኑን ምኒልክን ለዐፄ ቴዎድሮስ አሳልፎ ለመስጠት ተገደደ፡፡ ይኸም ኾኖ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ አንኮበር ከተማ ለመግባት አንጎለላ ላይ ከኦሮሞ ጦር ጋር ከፍተኛ ውጊያ ማድረጋቸው አልቀረም፡፡ ለወራት የዘለቀ ውጊያ አድርገው ሸዋን አስገብረው በጎጃም በኩል ወደ ጎንደር ተመለሱ (ባሕሩ፣ ፳፫ሺ)፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ዘምተው በማስገበራቸው በሚከተለው ግጥም ተሞግሰዋል፡፡

ሺ ዳለች ሺ ቦራ ነበር የሸዋ ፈረስ፣
አንድ ጥርኝ ኾነ ቢዘልቅ ቴዎድሮስ፡፡

በሙገሳ ግጥሙ ሠም የተገለጸው ዳለች (ቡላ ፀጉር ያለው ፈረስ) እና ቦራ (ግንባሩ ላይ ነጭ ፀጉር ያለው ፈረስ) መልክ ያለው የሸዋ ፈረስ ቁጥሩ ብዙ ነው፤ ኹለት ሺ ይኾናል፡፡ ነገር ግን፣ ብዛት ያለው የሸዋ ፈረስ ወደ አለበት ቴዎድሮስ ብቅ ሲል ወደ ጥርኝነት (ግራጫ ወይም ነጭና ጥቁር ፀጉር ወደ አለው ፈረስ) ተለወጠ፤ ብዙ የነበረው የሸዋ ፈረስ በቴዎድሮስ ፊት አንድ ብቻ ኾነ የሚል ነው፡፡

በወርቁ የተነገረው ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ሙገሳ ዋና መልእክት በዳለች ፈረስ የሚዋጋ የሸዋ መሳፍንትና መኳንንት አንድ ሺ ጦር፣ እንደዚሁም በቦራ ፈረስ የሚዋጋ አንድ ሺ ጦር በጠቅላላው ኹለት ሺ ፈረሰኛ ጦር ለውጊያ ተሰልፏል፡፡ ይኽን ያኽል ብዛት ያለው የሸዋ ፈረሰኛ (ጦር) ቴዎድሮስ በአንድ ጥርኝ ፈረሳቸው[25] ሊወጉት ሲመጡ፣ በፍርሃት ርዶ እፍኝ የማይሞላ ትንሽ (ጥርኝ) ኾነ፡፡ ከፍተኛ ቁጥር የነበረው የሸዋ ጦር ከተገመተው በታች ተዋጋ፤ በቀላሉ በቴዎድሮስ ጦር ድል ተመታ ማለት ነው፡፡ ይኽም፣ የቴዎድሮስን ጀግንነት ከፍ ያደርጋል፤ ያሞግሳል፤ የተቀናቃኞቻቸውን የሸዋ መሳፍንትና መኳንንት ደግሞ መዋጋት፣ መመከት በሚገባቸው ደረጃ አልተዋጉም፣ አልመከቱም በማለት ያኰስሳል፤ ዝቅ ያደርጋል፤ ይሰድባል፡፡ በቃል ግጥሙም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ሲሞገሱ፣ የሸዋ ጦር ደግሞ ተንኳሷል፣ ተንቋል፤ ተሰድቧል፡፡ የሙገሳ ግጥሙ ሳይዋጉ እጃቸውን ለዐፄ ቴዎድሮስ የሰጡ፣ በቀላሉ የተሸነፉና በፍርሃት የራዱ[26] ነበሩ የሚልን ታሪክ ያጎላል፡፡ የሙገሳ ግጥሙ ዐፄ ቴዎድሮስ በተወሰኑ አጋጣሚዎች በመንዝ፣ በግድምና በኤፍራታ የነበሩ ገዢዎች ሳይዋጉ እጃቸውን በመስጠታቸው በቀላሉ ባገኙት ድል ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ሙገሳው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተከታታይ ወደ ሸዋ ዘምተው ባካኼዷቸው ውጊያዎች ያጋጠሟቸውን ጠንካራ የመከላከል ርምጃዎች በትክክል አይገልጽም፡፡

የሙገሳ ግጥም ከተመሠረተበት ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው በዐፄ ቴዎድሮስ በቀላሉ ያልተሸነፉ፣ ከፍተኛ የመከላከል ጦርነት ያካኼዱ መሳፍንትና መኳንንት ነበሩ፡፡ በመጀመሪያው ዘመቻ ለወራት የዘለቀ መከላከል አድርገዋል፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለኹለተኛ ጊዜ ወደ ሸዋ የዘመቱት በመርሐ ቤቴው ገዢ በአቤቶ ሰይፈ ሥላሴ የሚመራ አማጺ ቡድን የአንኮበር ከተማን ተቆጣጥሮ በእሳቸው የተሾሙትን አስተዳዳሪዎች በማባረሩ ነበር፡፡ በዚኽ ዘመቻ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የሚመራው ጦር የአንኮበር ከተማን ለመቆጣጠር ያደረገውን ተደጋጋሚ ሙከራ በአቤቶ ሰይፉ የሚመራው ጦር ተከላክሎ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ (ዊዳሌ፣ 1904)፡፡ "ንጉሡም የዚህን ጦርነት በአቤቶ ሰይፉ ቢያዩ እንደ እነዚህ ያሉት በፊት [የመጀመሪያው የሸዋ ዘመቻ] ተገኝተው ቢሆን ሸዋን አላያትም ነበር፡፡ የወታደር ሙያ በአንኮበር ብቻ ይቆጠር አሉ፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ አልቀረምና አቤቶ ሰይፉ የቴዎድሮስን ወሬ ሲሰሙ [ጦሩን የሚመሩት ቴዎድሮስ መኾናቸውን ሲሰሙ] ሰዌን አላስጨርስም ብለው ከተማውን ለቀው ወደ ታች ወረዱ" (ዊዳሌ፤ 1904፤ 20-21)፡፡ በዚኽ ጊዜ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጦር በአቤቶ ሰይፈ ሥላሴ የሚመራውን ጦር ማጥቃትና ማሳደድ ቀጠለ፡፡ አንኮበርንም በእጁ አስገባ፡፡ ከአቤቶ ሰይፉ ጎን የተሰለፉትን ወታደሮች ብቻ ሳይኾን በካህናቱም ላይ ቅጣት ፈጽመው ወደ መቅደላ ተመለሱ፡፡

---

[25] ቃል ግጥሙ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን በተባዕታይ ፆታ ነጠላ ቁጥር ይጠራል፡፡ በጽሑፍ ግን በአክብሮት ተጠርተዋል፡፡ ይኽ የተደረገበት ምክንያት ባህሉን መሠረት በማድረግ በጥናቱ በወጥነት በአክብሮት ለመጥራት ታስቦ ነው፡፡

[26] "ልደትን ጥምቀትን ከኦሮሞው [ስሙ ከቅርብ ጊዜ ወዲኽ የተመረጠውን የተከተለ ነው፡፡] አገር ዋሉ፡፡ ስለክብረ በዓል ብዙ ነፍጥ አስተኰሱ፡፡ ያነግዜም ብዙ ኦሮሞ [ተ]ሰልፎ በዕሩቅ ቁሞ ነበር፡፡ የነፍጡ ድምጥ እጅግ በበዛበት ጊዜ ሁሉም ሸሸ፡፡ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገና አስቀድሞ ሲወርዱ፡፡ በኦሮሞው ሰልፍ ማኽል በፈረስ ብቻዎን በገቡ ጊዜ ሁሉም ይሸሻል፡፡ የድኃ ልብስ ለብሰው ተሰውረውም በገቡበት ጊዜ ሁሉ ይሸሽ ነበረ፡፡ ያውቃቸውማል፡፡ የእግዚአብሔር ኀይል አድሮብዋልና፡፡ አንዱ ሺውን ያሸሻል እንዳለ መጣፍ" (ሊትማን፣ 1902፤ 24)፡፡ የሙገሳ ግጥሙ ይኽንን ታሪክ መሠረት ያደረገ ይኾን? ሚል ጥያቄ ያስነሣል፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በመጀመሪያውም፣ በኹለተኛውም ዘመቻዎች የተራዘመ ጦርነት አካኺደው ሸዋን አስገበረዋል፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ ሸዋን እንዲያስተዳድሩ የሾሙዋቸው በዛብህ በማመጻቸው ወደ ሸዋ ዘመቱ፡፡ አፍቀራ የመሸጉትን በዛብህን ለማጥቃት ቢሞክሩም ጉልበታቸው እንደቀደመው ያልነበረው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ሊሳካላቸው አልቻለም፡፡ ለማጥቃት ተደጋጋሚ ሙከራ አድርገው አልሳካላቸው በማለቱ ፊታቸውን አዙረው ወደ መቅደላ ተመለሱ (ሊትማን፣ 1902፤ Darkwah, 1969)፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተለያዩ መሳፍንት የተከፋፈለችውን ኢትዮጵያን በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር እንድትመራ የማድረግ ዓላማቸውን ለመተግበር መጣራቸውና ለዓላማቸው እንቅፋት ለመፍጠር የሞከሩትን አማጽያንንና ተባባሪዎቻቸውን በማሸነፋቸው ተሞግሰዋል፡፡ ከተሞገሱባቸው ግጥሞች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡

> የሸዋ የጎዣም ተበትኖ ከብቱ፣
> የወሎ የትግሬ ተበትኖ ከብቱ፣
> ገዛው አባ ታጠቅ ሰብስቦ በሀብቱ፡፡ (ማኅተመ ሥላሴ፣1961፤ 245)

በግጥሙ ሥም የተነገረው አባ ታጠቅ የሸዋን፣ የጎጃምን፣ የወሎንና የትግራይን ከብት በሙሉ በገንዘባቸው ገዙት፤ ጠቀለሉት፣ ላሙም፣ በሬውም ከእሳቸው ቤት ይገኛል የሚል ነው፡፡ በሥሙ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተሞገሱት በግጥሙ የተጠቀሱትን ክፍለ ግዛቶች ከብት ጠቅልለው በመግዛታቸው ሀብታም በመኾናቸው ነው፡፡ ይኹን እንጂ በታሪክ እንደሚታወቀው ዐፄ ቴዎድሮስ በተጠቀሱት ክፍለ ግዛቶች የነበሩትን ላሞችና በሬዎች በገንዘባቸው ገዝተው የራሳቸው ሀብት በማድረግ አይታወቁም፡፡ እሳቸው የሚታወቁት ዛሬ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ትግራይ፣ ወሎና ሸዋ ተብለው የሚጠሩትን ከመሳፍንቱ ግዛትነት አስለቅቀው አንድ አድርገው በመግዛትና በማስገበር ነው፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እነዚኽን ቦታዎች ይገዙ የነበሩትን መሳፍንት በመውጋትና በማሸነፍ የኢትዮጵያን አንድነት መሠረት በመጣል በታሪክ በመልካም ይወሳሉ፡፡ ይኽም ገዛው በሚለው ቃል በወርቁ የተጠቀሱትን ክፍለ ግዛቶች በጦር ኀይል አሸንፈው በመያዛቸው፣ በማስገበራቸው፣ በማስተዳደራቸው፣ በመምራታቸው፤ ጠቅልለው በመግዛታቸው አንድነትን ለመፍጠር ጥረት በማድረጋቸው አባ ታጠቅ ተሞገሱ፡፡ የተበታተነ የከብት መንጋ በእረኛ እንደሚሰበሰበው ኹሉ፣ በመሳፍንቱ ተነጣጥለው የነበሩት የኢትዮጵያ ክፍላተ ግዛትም በዐፄ ቴዎድሮስ አንድ ተደርገዋል፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የአንዱን መስፍን ግዛት ይዘው በቃኝ አለማለታቸውን የሚያሞግስሐሳብ ሲነገር ሲሰሙ ከፍተኛ ደስታ ይሰማቸው እንደ ነበር ከሚከተለው የአዝማሪ ግጥም እንረዳለን፡፡

ቴዎድሮስን ባል ብሎ ማን አምኖ ይቆርባል፤[27]
ሴሰኛውን ጎበዝ ያራቱን ማእዘን ባል፡፡
(ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ 2002፤ 151)

ሙገሳው የተዜመው እሳቸው ግብር በሚያበሉበት አጋጣሚ ነው፡፡ ይኸውም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ኹሉም የሸዋ መኳንንት እርሳቸው ዘንድ እንዲቀርቡ ትእዛዝ ያስተላልፋሉ፡፡ በትእዛዙ መሠረት አቦዬ ለዐፄ ቴዎድሮስ ግብር ይዘው ይኼዳሉ፡፡ በዛብህ ግን ሀገር እንዲጠብቁ ተብሎ ወደ ግብሩ ቦታ ሳይኼዱ ይቀራሉ፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም "እሾማለሁ" በማለት ለኼደው መኳንንት ግብር በሚያበሉበት አጋጣሚ ላይ አዝማሪ እሳቸው የኢትዮጵያን አንድነት ለመፍጠር የሚያደርጉትን ጥረት በማድነቅ በተጠቀሰው ግጥም አሞግሷቸዋል፡፡

በዚኽ ስሙ ባልተገለጸ አዝማሪ የተዜመው የሙገሳ ግጥም መልእክት የተነገረው በሠምና ወርቅ ነው፡፡  በሠሙ አዝማሪዉ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ይሰድባል፡፡ ስድቡም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዘማዊ በመኾናቸው በኹሉም አቅጣጫዎች (በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅና በምዕራብ) ሚስት ማግባታቸው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ቀኖና ተቃራኒ ተግባር በመፈጸማቸው ነቅፏቸዋል፡፡ እንዲኽ ዓይነት ጥፋት የፈጸሙ ሰውን በማመን በአንድ የትዳር ጓደኛ መወሰን የሚፈቅደውን ቁርባን ለመቀበል አይቻልም፡፡ የትዳር ሕይወትን በቁርባን ወይም በሥጋ ወደሙ ለመወሰን፣ ከትዳር በላይ ማመንዘርን መተው ግድ የሚለውን ተግባር ያከብራሉ ተብሎ አይታመንም፡፡ "የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማዕድ" እንደሚባለው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ሚስት የማብዛት ባሕርያቸውን አይተዉም የሚል ሥጋት ስለሚፈጥር አምኖ መቁረብ አይቻልም፡፡ ይኽ የአመንዝራነት ባሕርይ እያለባቸው ከእሳቸው ጋራ በቁርባን ለመወሰን አይቻልም፡፡ ከአንደኛዋ ሚስታቸው ጋር ቢቆርቡም በተለያዩ ቦታዎች ወደሚኖሩት ሚስቶቻቸው መኼዳቸው፣ ዝሙት መፈጸማቸው አይቀርም፡፡ እንዲኽ ዓይነት ተግባር ከሚፈጽሙት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጋር ለመቁረብ የእምነቱ ቀኖና አይፈቅድም፡፡ የሴሰኛነት ባሕርይ ካለባቸው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጋር መቁረብ አይታሰብም በማለት በሠሙ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ሰብእና፣ ዝቅ አድርጓል፤ አዋርዷል፡፡

ይኹን እንጂ አዝማሪው ገድሎ ማዳን በሚሉት ዘዴ ዐፄ ቴዎድሮስን በወርቁ አሞግሷል፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተሞገሱት ሴሰኛ፣ ማዕዘንና ባል በሚሉት ቃላት አማካኝነት ነው፡፡ ሴሰኛ የሚለው ቃል በግጥሙ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም የሚያመሠጥረው ማመንዘርን፣ መሸርሞጥን ሳይኾን፣ አንድን ነገር ለመፈጸም፣ ለማከናወን ከፍተኛ ፍላጎት፣ ጉጉት ማሳየትን፣ በአንድ ነገር

[27]ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በሥርዓተ ንግሣቸው "ከሚስታቸው ከወይዘሮ ተዋበች ጋር "ቆርበው ሠራዊትዎንም "ያልቆረብህ እጠላኃለሁ" ብለው ዓዋጅ ቢነግሩ ከሰራዊትዎም ከመኳንንትዎም በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር የመረጣቸው እየተገኙ ቆረቡ የመንግሥትም ሥርዓት ወሬ በየሀገሩ ተነገረ፡፡" ለቤተ ክህነት ኀላፊዎችና ለተከታዮቻቸው መቁረብ ለምን እንዳስፈለጋቸው በእግዚአብሔር ሥርዓት መኖር የሱን ይቅርታ፣ ማለትም ለሕዝብና ለአገር ሰላም፣ ያስገኛል በማለት አስረዱ፡፡ ኋላ በ1862 ለእንግሊዝ ንግሥት ለቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ ኢትዮጵያ በውስጥ ችግሮች የታወከችውና በውጭ ጠላቶች የተደፈረችው የእግዚአብሔርን ሥርዓት ባለመከተላቸው ነበር ብለው ገልጸዋል፡፡" (መርዕድ፣ 1990፤ 98)፡፡

አለመርካትንና አለመወሰንን ወይም አለመታቀብን ነው፡፡ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት መሳፍንቱን ወግተውና አሸንፈው ሀገርን አንድ አድርገው ለመምራት መጣራቸው፣ መድከማቸው ነው፡፡ ስለኾነም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ሴሰኛ ያስባላቸው እንደ ዘመኑ መሳፍንት ገዢዎች ግዛታቸውን በአንድ ቦታ አለመወሰናቸው በአራቱም አቅጣጫዎች የሚገኙትን የተጠቀሱትን ግዛቶች ጠቅልለው ለመግዛት መፈለጋቸው ነው፡፡

ማዕዘን የሚለው ቃል በግጥሙ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም አቅጣጫ ማለት ነው፡፡ አራቱም ማዕዘን የሚለውም ከቋራ ምዕራብ፣ ምሥራቅ፣ ሰሜንና ደቡብ አቅጣጫዎች የሚገኙ ቦታዎች ማለት ነው፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከቋራ ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኘውን የፉንጅ ከተማ ስናርን የመያዝ ምኞት እንደ ነበራቸው፡-

አሽከሩ ገብርዬ በቅሎው አማረች፣
ፊቷን ወደ ስናር ዞራ ታያለች፡፡ (ገሪማ፣1996፤ 187)

በማለት አዝማሪ አብተው ምኞታቸውን በመደገፍ ገጥሞላቸዋል፡፡ እሳቸው ቱርኮች የሚሏቸው ግብፆች ከመንገሳቸው በፊት ያደረሱባቸውን ጥቃት የመበቀልና የያዙትን ቦታ የመንጠቅ ሐሳብ ነበራቸው፡፡ ከቋራ ተነሥተው ወደ ምሥራቅ በመኼድ በጌምድርን፣ ላስታን፣ ዋድላን፣ የጁን፣ ቤተ ዐማራንና ወረሂመኖን ጠቅልለዋል፡፡ ወደ ደቡብ ዘምተው ጎጃምን፣ ዳሞትን ከዚያም አልፎ ሸዋን አስገብረዋል፡፡ ወደ ሰሜን ዘምተው ደጅ አዝማች ውቤን ወግተውና አሸንፈው ግዛታቸው የነበሩትን ከወገራ እስከ ሐማሴን ጠቅልለዋል፤ አስገብረዋል፡፡

ባል የሚለው፣ የበላይነትን፣ የአዛዢነትንና የገዢነትን ተግባር ይገልጻል፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የአራቱም ማዕዘን ባል የመባላቸው ምክንያትም፣ በዘመነ መሳፍንት ይገዙ የነበሩትን በተለያዩ አቅጣጫዎች የመሳፍንቱን ግዛቶች ኹሉንም አሸንፈው ግዛቶቻቸውን አንድ አድርገው በበላይነት ማስተዳደራቸው፣ መግዛታቸው፣ መምራታቸው፣ ፍትሕና ርትዕ ለመስጠት መጣራቸው ነው፡፡ በመኾኑም፣ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የመግዛት ፍላጎታቸውን አንድ መስፍን ይገዛው በነበረ ቦታ አለመወሰናቸው፣ የተለያዩ መሳፍንት ይገዟቸው የነበሩትን በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚገኙ ግዛቶችን ጠቅልለው መግዛታቸው በአዝማሪ አስሞግሷቸዋል፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተለያዩ ግዛቶች የነበሩትን መሳፍንት ወግተው ድል በማድረጋቸው በአዝማሪ ከተሞገሱባቸው ግጥሞች መካከል፡-

የኢትዮጵያ መሳፍንት ቅስና ቢያምራቸው፣
ካሣ ጳጳስ ኾኖ ኹሉን ባረካቸው፡፡ (ገሪማ፣ 1996፤ 187)

የሚለው እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

የሙገሳ ግጥም መልእክት በሠምና ወርቅ የተነገረ ነው፡፡ በሠሙ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የነበሩ መሳፍንት "የቅስና መዕረግ ማግኘት በመፈለጋቸው" "ጳጳሱ ዐፄ ቴዎድሮስ" እጃቸውን በመሳፍንቱ ራስ ላይ ጭነው ፈቅደውና ባርከው አቀሰሷቸው፤ የቤተ መቅደስ አገልጋዩ፣

*ባራኪ፣ ቀዳሽ፣ ናዛዥ፣ የነፍስ አባት እንዲኾኑ መንፈሳዊ ሥልጣን ሰጧቸው ማለት ነው፡፡ መንፈሳዊ ሥልጣን መስጠት የቻሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከኤጲስቆጶስ በላይ ከሊቀጳጳስ በታች የኾነ መንፈሳዊ አባትነት ሥልጣን ስለ አላቸው፣ ጳጳስ በመኾናቸው ነው ማለትን ይገልጻል፡፡ ይኽ በሠሙ የተገለጸው ተግባር የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን እውነተኛ ማንነት አይገልጽም፡፡ እሳቸው በታሪክ የሚታወቁት በመንፈሳዊ አባትነት ሳይኾን ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ለመግዛት መሳፍንቱን ወግተው በማሸነፍ ሀገራዊ አንድነትን ለመመሥረት ጥረት በማድረግ ነው፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ መሳፍንቱን በማሸነፍ በፈጸሙት የጀግንነት ተግባር ከተሞገሱባቸው ግጥሞች መካከል የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡*

*አባ[28] ታጠቅ ካሣ ሱሪ መስፋት ሲያውቁ፣*
*ገጣጥመው ሰፉና ኹሉን አስታጠቁ፡፡*
(*ገሪማ*፣ 1996፤ 186 – 187)

*የሙገሳ ግጥሙ መልእክት በሠምና ወርቅ የተነገረ ነው፡፡ የሙገሳ ግጥም ሠምና ወርቅ የተነገረው አስታጠቁ በሚለው ቃል ነው፡፡ ቃሉ በሠሙ አባ ታጠቅ ተብለው በፈረስ ስማቸው የተጠሩት ዐፄ ቴዎድሮስ የተሞገሱት ሱሪ የመስፋት ዕውቀታቸውንና ችሎታቸውን ተጠቅመው ሱሪ ሰፍተው ኹሉንም ማልበስ በመቻላቸው ነው፡፡ ሱሪ ለመስፋት ለዚኹ የሚኾንን ጨርቅ በተለያየ መጠን መቆራረጥንና የተቆረጡትን ውበትና አገልግሎት እንዲኖራቸው አድርጎ መስፋትን ይጠይቃል፡፡ ሙገሳው የተነገረባቸው ሐረጎች ገጣጥመው ሰፉና ሱሪ ማስታጠቅ የሚሉት ናቸው፡፡ ይኹን እንጂ በግጥሙ አባ ታጠቅን ማሞገስ የተፈለገው ሱሪ ሰፍተው ሌላውን ሰው በማልበሳቸው እንዳልኾነ እሳቸው ከነበራቸው ፖለቲካዊ ሥልጣን ጋር እንደማይጣጣም ከታሪካቸው እንረዳለን፡፡*

*አባ ታጠቅ የተሞገሱት "ገጣጥመው ሰፉና ኹሉን አስታጠቁ" በሚለው ኹለተኛው ሥንኝ ነው፡፡ "ገጣጥመው ሰፉ" በሚለው የመጀመሪያው ሐረግ ሙገሳው የተገለጸው በንጽጽር ነው፡፡ አንድ የነበረ ጨርቅ መቆራረጡ፣ አንድ ሀገር የነበረችው ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት ከመከፋፈሏ ጋር ይነጻጸራል፡፡ የተቆራረጠው ጨርቅ ተገጣጥሞ መሰፋቱ፣ ለገመና መሸፈኛና ለማጌጫ የሚያገለግል ሱሪ መኾኑ ደግሞ በዘመነ መሳፍንት ተከፋፍላ የነበረችው ኢትዮጵያ በአባ ታጠቅ ካሣ አንድ እንድትኾን ከመደረጉ ጋር ተነጻጽሯል፡፡ ኢትዮጵያ አንድ እንድትኾን መደረጉም በመሳፍንቱ መካከል በግዛት ይገባኛል ወይም ገብር አልገብርም በሚል ጦርነት መግጠማቸው ተጎጂው ድኻው ሕዝብ ነው፡፡ አርሶና ነግዶ የሚኖረው ሕዝብ ሳይፈልግ እንዲዘምትና እንዲዋጋ ይደረጋል፤ ተሠሪ እንዲያስተናግድ ይገደዳል፤ የራሱ ቤት ባይተዋር ይደረጋል፤ ወታደር ጦም አሳድረኻል በሚል ሰበብ ይቀጣል፡፡ የተለያዩ ክፍለ ግዛቶችን የሚገዙትን መሳፍንት በማሸነፍ ኢትዮጵያ በአንድ ንጉሥ እንድትመራ ማድረግ የድኻውን መከራ ያስቀራል፤ ለድኻው አንጻራዊ*

---

*[28]አባ የሚለው ቃል በሙገሳ ግጥሙ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም የታጠቅ ባለቤት፣ የታጠቅ ጌታ ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያን ነገሥታት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን፣ አባ ታጠቅ፤ ዐፄ ዮሐንስን፣ አባ በዝብዝ፤ ዐፄ ምኒልክን፣ አባ ዳኘው፤ ዐፄ ኃይለ ሥላሴን፣ አባ ጠቅል ብሎ መጥራት የተለመደ መኾኑን ልብ ይሏል፡፡ ቃሉ እያንዳንዳቸው በስም የተጠራው ፈረሳቸው ጌታ መኾናቸውን ይገልጻል፡፡*

እፎይታን ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡ አባ ታጠቅ የተሞገሱት በታሪክ የሚታወቀውን በዘመነ መሳፍንት በተለያዩ ክፍለ ግዛቶች ተከፋፍላ የነበረችውን ኢትዮጵያን አንድ በማድረጋቸው የጦርነቱ ሰለባ የመሳፍንቱ ወታደሮች ጥቃት ተሸካሚ የሚኾነው መከራ የሚቀንስ ተግባር ፈጽመዋል ፡፡

“አስታጠቁ” የሚለው ቃል በወርቁ ሦለት መልእክቶች ተገልጸውበታል፡፡ አንደኛው አባ ታጠቅ ካሣ በመሳፍንቱ በደል የደረሰበትን የኅብረተሰብ ክፍል ለተፈጸመበት ክፉ ድርጊት ምላሹን ሰጡለት፣ ተበቀሉለት፣ ክፉን በክፉ መለሱለት ማለት ነው፡፡ ይኸም “አስታጠቁ” በሚለው ቃል አባ ታጠቅ ጦራቸውን አደርጅተው በደል ይፈጽሙ የነበሩትን መሳፍንት ወግተው በማሸነፍ፣ በኀይላቸውና በጉልበታቸው ገትተው በድኻው ላይ ይደርስ የነበረውን በደል በማስቆማቸው በመታደጋቸው ኩራትን በማስገኘታቸው ነው፡፡ መሳፍንቱ በድኻው ላይ ይፈጽሙ የነበሩትን በደል ያስቀሩትና ደጋፊዎቻቸውን ጭምር ያስደሰቱና ያኮሩት በኀይላቸውና በጉልበታቸው በመኾኑ ለመሞገሻቸው ምክንያት ነው፡፡ ኹለተኛው ሱሪ ሰፍተው ማልበሳቸው በእርሳቸው ውስጥ ያለውን ጀግንነት፣ ድፍረት፣ አሸናፊነትና ወኔ ለሌሎች በማላበስ በበደሏቸው ላይ ጀግና እንዲኾኑ አድርገዋል ማለትም ነው፡፡ ሦስተኛው በወርቁ የተነገረው መልእክት አባ ታጠቅ ካሣ በተለያዩ ክፍለ ግዛቶች ተከብረውና ኰርተው ይኖሩ የነበሩትን መሳፍንትና መኳንንት ወታደር አዝምተው ወግተው አሸንፈው፣ የአመጹባቸውንም ቀጥተው ለእሳቸው ልብሳቸውን አሸርጠው፣ አደግድገው ለብሰው እጅ እንዲነሡ አደረጉ ማለት ነው፡፡ የተሞገሱት መሳፍንቱን በጀግንነት አሸንፈው ኢትዮጵያን አንድ በማድረጋቸው የበላይነታቸውን ያገኙት በጀግንነታቸው በወንድነታቸው ነው፡፡ አባ ታጠቅ ካሣን ያስሞገሳቸው በጀግንነታቸውና በወንድነታቸው መሳፍንቱን አሸንፈው ኢትዮጵያን በበላይነት መምራታቸውና ማስተዳደራቸው ነው፡፡

3) **መደምደሚያ**

ይኸ ጥናት ትኩረት ያደረገባቸው የሙገሳ ግጥሞች በጽሑፍ ተመዝግበው የተገኙ እንጂ ሙገሳዎቹ በተከውኑባቸው አጋጣሚዎች ላይ የተሰበሰቡ አይደሉም፡፡ በአዝማሪ መዜማቸውን የገለጹትም የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕሎች ጸሓፊዎች፣ ታሪካቸውን ያጠኑ ሰዎችና ሰለእሳቸው አጫጭር መረጃዎችን የሰጡ ሰዎች ናቸው፡፡ አዝማሪ በሚኖርባቸው አካባቢዎች (አማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያ፣ አገው፣ ወዘተርፈ) የሙገሳ፣ የፍቅርና ሌሎችንም ግጥሞች የሚደርስበትና የሚከውንበት ባህል የሚሰጠውን ሙብት ለመገንዘብ ተሞክሯል፡፡

ለልጅ ካሣ/ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በአዝማሪ የተደረደሩላቸው ሙገሳዎች በወታደራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴአቸው ስኬቶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተሞገሱባቸው ግጥሞች በኹለት ምዕራፎች ላይ ያተኩራሉ፡፡ የመጀመሪያው፣ እቴጌ መነን በጎንደር ቤተ መንግሥት ተቀምጠው የቋራ ምስለኔ ኾነው እንዲሠሩ ምኞት ያልሰጣቸው ልጅ ካሣ “ክብር አልተሰጠኝም” በማለት አኩርፈው ከቤተ መንግሥቱ ርቀው ወደ ቋራ ወርደው ሸፈቱ፡፡ በድርጊቱ የተቆጡት እቴጌ መነን ወታደር አዘመቱባቸው፡፡ ልጅ ካሣ የዘመተባቸውን ጦር ድል አድርገው

ጦር መርቶ የመጣወውን ማርከው በሞት ቀጡት፡፡ ልጅ ካሣ ያልተገመተ ድል በማግኘታቸው ጀግና አስባላቸው፤ አስሞገሳቸው፡፡ ያዘመቱት ጦር መሸነፍ የተበሳጨት እቴጌ መነን ጦር አብዝተው ድጋሜ አዘመቱባቸው፡፡ ልጅ ካሣ በድጋሜ ድል አደረጉት፡፡ ለልጅ ካሣ የተሳሳተ ግምት የነበራቸው እቴጌ መነን ጦር መርተው ዘመቱባቸው፡፡ የድል በር የተከፈተላቸው ልጅ ካሣ፣ በእቴጌ መነን የተመራውን ጦር ድል አድርገው እሳቸውንም ማረኩ፡፡ በእናታቸው መማረክ የተበሳጨት ራስ ዓሊ እናታቸውን ለማስፈታት ከልጅ ካሣ ጋር መደራደር ግድ ኾነባቸው፡፡ ልጅ ካሣን ደጅ አዝማች ብለውና ግዛት አስፍተው በመስጠት እናታቸውን አስፈቱ፡፡

ደጅ አዝማች ካሣ ከፍርቃ በታች ያለውን ግዛት ከራስ ዓሊ ሲቀበሉ በጀግንነታቸውና በወታደራዊ አቅማቸው በግንባር ቀደምነት ከሚጠሩት ከዳሞቱ ጎሹ ጋር ተፋጠጡ፡፡ ቆይቶም ደጅ አዝማች ጎሹ ደጅ አዝማች ካሣን ለመውጋት ዘመቱ፡፡ በኹለቱ መካከል በተደረገው ጦርነት ድሉ የደጅ አዝማች ካሣ ከመኾኑም በላይ ደጅ አዝማች ጎሹ ተገደሉ፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ወደ ከፍተኛው የሥልጣን ደረጃ ለመሸጋገር አይሻል ላይ ወደ ነበሩት አማታቸው ራስ ዓሊ ዘምተው ድል አድርገው አባረሯቸው፡፡ በጎጃም ላይ የአባትና ልጁ (የደጅ አዝማች ጎሹ ዘውዴና የደጅ አዝማች ብሩ ጎሹ) ባላንጣ የነበረውን ተድላ ጓሉን ሾሙ፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ በጉር ዐምባና በአይሻል በተከታታይ ከፍተኛ ድሎችን በማግኘታቸው በአዝማሪ አብተው ተሞገሱ፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ወደ ሰሜን ዘምተው ደጅ አዝማች ውቤን ድል አድርገው ነገሡ፡፡ አመጽ ከጀመሩበት ከቋራ ተነሥተው፣ በጎጃምና በሰሜን ተደጋጋሚ ድሎችን በመጎናጸፋቸው በአዝማሪ ሙገሳ ተቸራቸው፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተሞገሱባቸው የሕይወታቸው ኹለተኛ ምዕራፍ በኾነው የንግሥና ዘመናቸው መሞገሳቸው ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ ደጅ አዝማች ውቤ ይገዙት የነበረው በተለይም የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የሰሜንና የአርማጭሆ ሕዝብ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን አሸናፊነት አምኖ መገዛቱን በግጥም ገለጸ፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ትኩረታቸውን በወሎና በሸዋ መሳፍንት ላይ አደረጉ፡፡ ወሎን በኀይል አስገብረው ወደ ሸዋ ተሻገሩ፡፡ ለመከላከል የሞከሩትን የንጉሥ ኀይለ መለኮት ደጋፊዎች አሸንፈው ሸዋን እንዲገብር አደረጉ፡፡ በወሎ፣ በሸዋና በጎጃም ያመጹባቸውን ለመቅጣት ደጋግመው ዘመቱ፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ መሳፍንቱን ድል በማድረጋቸውና በማስገበራቸው አዝማሪ ሙገሳ አልነፈጋቸውም፡፡ እሳቸው ወሎንና ሸዋን ለማስገበር በዘመቱባቸው ጊዜያት በሰሜንና በትግራይ ጋረድ፣ ደጅ አዝማች ንጉሤና ፊታውራሪ ተሰማ ሸፍተው አንገብርም አሉ፡፡ እሳቸውም ከሸዋ ወደ ሰሜንና ወደ ትግራይ በመዝመት ያመጹትን ወግተው ድል አደረጓቸው፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ፊታቸውን ወደ አንድ አቅጣጫ አዙረው ተቀናቃኞቻቸውን ለመውጋት ሲዘምቱ ባቀኑትና ባስገበሩት ክፍለ ግዛት ለአመጽ የሚነሣሡትን ኹሉ እየተመላለሱ ወግተው ድል በማድረጋቸው ከባድ ቅጣት በመቅጣታቸው፣ የመሳፍንቱን ግዛቶች ጠቅልለው ኢትዮጵያ የምትባል ሀገርን በመምራታቸው፣ የተለያዩ የለውጥ ርምጃዎችን በመውሰዳቸው አዝማሪ የተለያዩ የሙገሳ ግጥሞችን ደርድሮላቸዋል፡፡ ኹሉም የሙገሳ ግጥሞች በዚኽ ጥናት አልተተነተኑም፡፡

በአዝማሪ፣ በአስለቃሺና በሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን የሚያሞግሱ፣ የሚተቹና የኀዘን ስሜትን የሚገልጹ በርካታ ግጥሞች ተደርድረዋል፡፡ ስለእሳቸው የተደረደሩት ግጥሞች በተለያዩ ሰዎች ሥራዎች ሲመዘገቡ በአንዳንዶቹ ላይ ለውጥ ይስተዋልባቸዋል፡፡ ለውጡ እንዴትና በምን ምክንያት እንደተፈጠረ መመርመርና በመተንተን አስፈላጊ ነው፡፡ በተለያዩ ሰዎች ሥራዎች ተመዝግበው የሚገኙትን ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተገጠሙትን የቃል ግጥሞች ሰብስቦ ማጥናት ስለ እሳቸው በቃል ግጥም የተነገረውን ለመረዳትና ታሪካዊ እውነታው ምን ያኽል እንደተገለጸ ለማወቅ ያስችላል፡፡ ስለኾነም የቃል ግጥም ተመራማሪዎች፣ የቃል ታሪክ አጥኚዎች፣ የሥነቃልና የሥነ ግጥም ተማሪዎች ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙትን የተለያዩ የቃል ግጠሞች ትኩረት ሰጥተው ማጥናታቸው ተገቢ መኾኑን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

## መረጃ ጽሑፎች


ሊትማን፣ ኢኖ፡፡ 1902፡፡ *የቴዎድሮስ ታሪክ* ፡፡ ፕሪንስቶን፤ ሻርልስ ስክሪብኔር ልጆች፡፡

መርዕድ ወልደ አረጋይ ፡፡ 1990 (እ. አ. አ)፡፡ "የቴዎድሮስ ዓላማዎች ከየት እንደመነጩ"፡፡ In: KASA *AND KASA: Papers on the Lives, Times and Images of Tewodros II and Yohannes IV(1855-1889)*. (Edited by Taddese Beyene, Richard Pankhurst, Shiferaw Bekele) Addis Ababa: INSTITUTE OF ETHIOPIAN STUDIES, ADDIS ABABA UNIVERSITY, Pp. 69- 115.

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፡፡ 1961፡፡ *አማርኛ ቅኔ ከነ መፍቻው ተሻሽሎና ታክሎበት የተሰናዳ* አዲስ አበባ፤ እሌኒ ማ. ኃ. የ. ግ. ማ.፡፡

-------------፡፡ 1961፡፡ *ዝክረ ነገር*፡፡ አዲስ አበባ፤ ሴንተራል ማተሚያ ቤት፡፡

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፡፡ 2000፡፡ *ዳግማዊ ምኒልክ የአዲሱ ሥልጣኔ መሥራች*፡ (የታተመበት ቦታ ማተሚያ ቤቱና ዓመት ምሕረቱ አልተገለጸም) ፡፡

ሥርግው ገላው፡፡ 2008፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፡፡* (ሐተታ በሥርግው ገላው) አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ባሕሩ ዘውዴ፡፡ ፪ ሺህ፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከ1847 እስከ 1983*፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡ 1981፡፡ *ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት* ፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት (ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት)፡፡

አስቴር ሙሉ፡፡ 2007፡፡ "ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽንኮሌጅ፣ የአማርኛ የቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል (የሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፡፡

አዳነች አበራ፡፡ 2001፡፡ "የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መጻሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል (ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)፡፡

ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ 2000፡፡ *የመጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት* አዲስ አበባ (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም) ፡፡

------------- ፡፡ 1998፡፡ *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት* (8ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፡፡ 2006፡፡ *ኣማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ 1962፡፡ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ገሪማ ታፈረ፡፡ 1996፡፡ *አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ*፡፡ (ኹለተኛ እትም) አዲስ አበባ፤ Finfinne Printing and Publishing S. C.

ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ (ጸሓፌ ትእዛዝ)። ፲፱፻፵፱፡፡ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ገነት አየለ አንበሴ (ተርጓሚ)፡፡ 2009፡፡ *በኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች ቆይታዬ*፡፡ (የታተመበት ቦታ አልተገለጸም)፤ Graphic Printers.

Abrams, Lynn. 2010. *Oral History Theory*. London and New York: Routledge Taylor & Francis Group.

Ashenafi Kebede. 1975. "The "Azmari", Poet-Musician of Ethiopia," In፡ *The Musical Quarterly*. Vol. 61, No. 1, Pp. 47-57.

Ben-Amos, Dan. 1993. “"Context" in Context.” In: *Western Folklore, (Theorizing Folklore: Toward New Perspectives on the Politics of Culture)*, Vol. 52, No. 2/4pp. 209-226

Crummey, Donald. 1971. “The Violence of Tewodros.” In: *Journa of Ethiopian Studies*. Vol. 9, No. 2, Pp. 107-125.

---------------. 1969. “Tewodros as Reformer and Modernizer,” In: The Journal of African History. Vol. 10, No. 3, Pp. 457-469.

Darkwah, Kofi. 1969. “Emperor Theodore II and the Kingdom of Shoa 1855 1865.” In: *The Journal of African History*. Vol.10, No. 1, Pp. 105- 115.

Finnegan, Ruth. 1988. Literacy and Orality: Studies in the Technology of Communication. Oxford: Basil Blackwell.

---------------. 1977. Oral Poetry: Its nature, significance and social context. Cambridge, London, New York, Melbourne: canbridge University Press.

Fusella, Luigi. 1959. “La Cronaca dell' Imperatore Teodoro II di Etiopia in un manoscritto amarico,” *Annali dell' Instituto Universitario Orientali di Napoli*. Nuóva serie, Vol. VII, Pp. 63- 89.

---------------. 1958. “La Cronaca dell' Imperatore Teodoro II di Etiopia in un manoscritto amarico,” *Annali dell' Instituto Universitario Orientali di Napoli*. Nuóva serie, vol. VII, Pp. 69- 94.

Girma Getahun (translator). 2014. *The Goǧǧam Chronicle by Aläqä Täklä Iyäsus WaqGera*. Oxford University Press: The British Academy.

Hufford, Mary. 1995. “Context.” In: *The Journal of American Folklore*. Vol. 108, No. 430, Pp. 528-549.

Kimberlin, Cynthia T. 1983. “The Music of Ethiopia,” In: *Musics of many cultures: an introduction.* USA, Paperback Printing.

---------------. 1976. “Masinqo and the Nature of *Qañnat*.” A Dissertation Submitted in Partial Satisfaction of the Requirements for the Degree Doctor of Philosophy in Music, University of California, Los Angels.

Mitgeteilt, Mittwoch von Eugen Problem aus amharischem Volksmunde Pp. 33-35

Pankhurst, Richard and Asfaw, Girma-Selassie. 1985. “AN AMHARIC WAR SONG OF EMPEROR TEWODROS’S SOLDIERS.” In: *Journal of Ethiopian Studies*. Vol. 18, Pp. 51-62.

Shiferaw Bekele.1990. “Kassa and Kassa: The State of Their Historiography,” In: *KASA AND KASA: Papers on the Lives, Times and Images of Tewodros II and Yohannes IV (1855-1889)* (Edited by Taddese Beyene, Richard Pankhrst, shiferaw Bekele). Addis Ababa: INSTITUTE OF ETHIOPIAN STUDIES, ADDIS ABABA UNIVERSITY: Pp. 289-347.

--------.1990. "The State in the Zamane Masafent (1786-1855): An Essay in Reinterpretation," In: *KASA AND KASA: Papers on the Lives, Times and Images of Tewodros II and Yohannes IV (1855-1889)* (Edited by Taddese Beyene, Richard Pankhrst, shiferaw Bekele). Addis Ababa: INSTITUTE OF ETHIOPIAN STUDIES, ADDIS ABABA UNIVERSITY: Pp. 25- 68.

Vansina, Jan. 1985. Oral Tradition as History. London: The University of Wisconsin Press.

Vidailhet, Mondon C. 1904. *Chronique Theodoros II Roi des Rois d'ethipie (1853-1863) d'apres Un Manuscript Original Text Abyssin (Amharique)* (No place of publication and printing press).